በአትክልት ቀለሙ

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ክፍል
ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጹሑፍ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ሰኔ 2001

# በባህር ዳር ከተማ የአማራ ብሄራዊ ክልል ድምፅ መደበኛ ራዲዮ በሀሳብ ለሀሳብ የመዝናኛ ፕሮግራም አደረጃጀትና አቀራረብ በተመረጡ ናሙናዎች ምሳሌነት

በ
አትክልት ቀለሙ

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ክፍል
ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ

የጥናቱ አማካሪ
አለሙ ካሳዬ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ሰኔ 2001

## ምስጋና

በመጀመሪያ ይህ የአንተ ቦታ ነው ብሎ መርቆ ከትቢያ ጠርጎ ለሰጠኝ ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይግባው:: ምክንያቱም ለዚህች ቀንና እለት እንድበቃ አድርጎኛል::

በመቀጠልም ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል እንዳትክልት ኮትኩተህ ለፍሬ ለአበቃኸኝ ውድ አባቴ ቀለሙ አግዴ ውለታህን ለመክፈል ያንተን ጤና ያቆይልኝ:: እንዲሁም መቀነትሽን ታጥቀሽ አንጀትሽን አስረሽ የምበላውንና የምለብሰው ይቅር ብለሽ ላስተማርሽኝና ለዚህ ላበቃሽኝ ውድና እንቁ ለሆንሽኝ እናቴ ወ/ሮ ታምራለች ውቤ ከሁሉም ነገር ጤናሽን እየተመኘሁ ምስጋናዬ ከልብ ነው::

ሁሌም የእኔን ደስታ በጉጉት ለምትጠብቅኝ፣ አይዞህ ከጎንህ ነኝ እያልሽ ተስፋ ለሰጠሽኝ ውድ እህቴ አበራሽ ንጉሴ ምስጋናዬ ወሰን የለውም::

እንዲሁም ጥናቴ ፈር እንዲይዝ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል የማስተካከያ እርማት ለሰጡኝ አማካሪዬ ለአቶ አለሙ ካሳዬ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው::

በመቀጠልም እንደ እህት እንደ ወንድም የማይለኝ ውድ ጓደኛዬ እንዳለው አይታማ በሀሳብና በመረጃ እንዲሁም በገንዘብ ደግፈህ ጥናቱ የመጨረሻውን ውጤት ከዚህ እንዲደርስ ስለረዳኸኝ ከልቤ አመሰግንሃለሁ::

በመጨረሻም ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ክፍለ ትምህርት ተመራቂ ተማሪዎች፤ ቅድስት ተፈራ፣ አስካለ ግደይ፣ ንዋይ ጣልአርጌ እና በአጠቃላይ ለዲፓርትመንት ተመራቂ ተማሪዎች ላደረጋችሁልኝ መልካም ውለታ በእግዚአብሔር ስም ሁላችሁንም ከልቤ አመስግኛለሁ::

**አጠቃሎ**

ይህ ጥናት በባህር ዳር ከተማ በአማራ ብሄራዊ ክልል ድምፅ በ“ሀሳብ ለሀሳብ” የመዝናኛ ራዲዮ ፕሮግራም ከጥቅምት 1/2001 እስከ የካቲት 20/2001 ዓ.ም የተላለፉትን የፍቅር ግጥሞች፣ ቀልዶች፣ የፍቅር አባባሎች፣ ደብዳቤዎችና ሙዚቃዎችን ይዘትና ጥልቃቸውን ለመተንተን ተሞክሯል::

የ“ሀሳብ ለሀሳብ” የመዝናኛ ፕሮግራም በአንድ መልኩ ስለወጣቶች በፍቅር ዙሪያ የሚወያዩበትና የሚዝናኑበት የፕሮግራም አይነት ነው:: ይህም አጥኚውን ያነሳሱት ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፤ ወጣቶች በስልክና በደብዳቤ የሚሳተፉበት የፕሮግራም አይነት በመሆኑ ነው:: ስለሆነም አጥኚው ጥናቱን ከማጥናቱ በፊት በዚህ ፕሮግራም ተሳታፊ ስለነበር ሊያጠና ችሏል::

በመሆኑም በዚህ የመዝናኛ የራዲዮ ፕሮግራም የተላለፉትን በራዲዮ ጣቢያው ድምፅ ላይቭራሪ በመግባትና በማዳመጥ እንዲሁም ስለራዲዮ ፕሮግራም የሚያወሱትን መፅሀፍ በማንበብ ጥናቱ ውጤታማ ሆኖ እንዲጠና አጥኚውን ረድቶታል::

በመጨረሻም የራዲዮ አዘጋጆችን ቃለመጠይቅ በማድረግ በራዲዮ የድምፅ ላይቭራሪ በመግባት በማዳመጥና በመፃፍ 20 ያህሉን በፕሮግራሙ የተላለፉትን የፍቅር ግጥሞች፣ ሙዚቃዎች፣ የፍቅር አባባሎች፣ ደብዳቤዎችና ቀልዶችን በመሰብሰብ ከቅርፅና ይዘት አኳያ ሰፋ ያለ ማብራሪያ በመስጠት ለመተንተን ተሞክሯል::

## ማውጫ

**ርዕስ** **ገፅ**

ምዕራፍ አንድ.......................................................................................................... 1

1. መግቢያ ........................................ 7
1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........................................ 7
1.2. የጥናቱ ዳራ ........................................ 8
1.3. የጥናቱ አላማ ........................................ 9
1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................ 9
1.5. የጥናቱ ገደብ ........................................ 10
1.6. የጥናቱ ዘዴ ........................................ 10
1.7. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ........................................ 11
ምዕራፍ ሁለት ........................................ 11
2. ክለሳ ድርሳን ........................................ 11
2.1. የመዝናኛ ምንነት ........................................ 11
2.2. የራዲዮ መዝናኛ ፕሮግራም ምንነት ........................................ 12
2.2.1. ሙዚቃ ........................................ 14
2.2.2. ውይይት ........................................ 15
2.2.3. ደብዳቤ ........................................ 16
2.2.4. ግጥም ........................................ 16
2.3. የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ........................................ 18
ምዕራፍ ሶስት ........................................ 21
3. በ"ሀሳብ ለሀሳብ" በራዲዮ በተላለፉ የመዝናኛ ፕሮግራም የይዘት ትንተና ........................................ 22
3.1. በመዝናኛ ፕሮግራም የተነሱ አበይት ጉዳዮች ........................................ 22
3.1.1. የፍቅር ግጥሞች ........................................ 22
3.1.2. ቀልድ ........................................ 24
3.1.3. የፍቅር አባባሎች ........................................ 25
3.1.4. ደብዳቤ ........................................ 26
3.1.5. ሙዚቃ ........................................ 27

3.2. በ"ሀሳብ ለሀሳብ" በራዲዮ በተለላፍ የመዝናኛ ፕሮግራም የቅርጽ ትንተና ........................................ 30
3.2.1. የቃላት አጠቃቀም ........................................ 31
3.2.1.1. በፍቅር ግጥሞች ........................................ 31

3.2.1.2. ቀልዶች ........................................................................................ 34
3.2.1.3. የፍቅር አባባሎች.................................................................................. 35
3.2.1.4. ደብዳቤዎች......................................................................................... 37
3.2.1.5. ሙዚቃ ............................................................................................. 39
ምዕራፍ አራት.......................................................................................................... 43
ሀ. ማጠቃለያ............................................................................................................ 43
ዋቢ. መፅሀፍት
ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው
አባሪ ሀ
አባሪ ለ
አበሪ ሐ

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

ይህ ጥናት የተካሄደው በአማራ ብሄራዊ ክልል ድምፅ /መደበኛ ራዲዮ/ "በሀሳብ ለሀሳብ" በተሰኘ የመዝናኛ ፕሮግራም ላይ ነው:: በመሆኑም የዚህ ጥናት አቅራቢም የፍቅር ግጥሞችን፣ የፍቅር አባባሎችን እንዲሁም ሌሎች የመዝናኛ ፕሮግራሞች ከትምህርት ሰጭነታቸው በተጨማሪም አዝናኝነታቸው የጎላ በመሆኑ ለመመርመር ነው::

ጥናቱ በአራት ምዕራፎች የተከፋፈለ ነው:: በመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ገደብ፣ የጥናተ ዘዴ እና በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን የሚሉትን ይይዛል:: በምዕራፍ ሁለት የመዝናኛ ምንነት፣ በራዲዮ መዝናኛ ፕሮግራም ምንነትና የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት በተመለከተ ከዚህ ጥናት ጋር ዝምድና ያቸውን ጥናቶች ይዟል:: በምዕራፍ ሶስት በመዝናኛው ፕሮግራም የተላለፉትን የፍቅር ግጥሞች፣ የአድማጮች ደብዳቤ፣ ቀልዶች፣ የፍቅር አባባሎችና ሙዚቃዎችን ከይዘትና ከቅርፅ በመተንተን ተካተውብታል::እንዲሁም በምዕራፍ አራት የጥናታዊ ፅሁፍ ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳብ ቀርቧል::

### 1.1. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ፕሮግራሙን በማዳመጥበት ወቅት የሚተላለፍበት የአየር ሰአት አመች አለመሆኑ ነው:: በተጨማሪም "የሀሳብ ለሀሳብ" የራዲዮ ፕሮግራም በሚተላለፍበት ጊዜ ርዕሰ ጉዳዮቹ ግልፅነት ያላቸው በመሆናቸው ነው:: እንዲሁም በአማራ ብሄራዊ ክልል ድምፅ /መደበኛ ራዲዮ/ አድማጮች በይበልጥ የሚዝናኑበት የፕሮግራም አይነት የ"ሀሳብ ለሀሳብ" ፕሮግራም በመሆኑ

ነው:: ምክንያቱም ወጣቶች ሀሳባቸውን በነጻነት በሙዚቃ በደብዳቤና በስልክ ለ"ሀሳብ ለሀሳብ" ፕሮግራም በማድረስ የሚወያዩበት የፕሮግራም አይነት በመሆኑ ነው::

በተጨማሪም ይህ የራዲዮ ፕሮግራም ከሌሎች ፕሮግራሞች የሚለየው በክልል ደረጃ ከተቋቋሙት ማሰራጫዎች አንዱ በመሆኑ ነው:: እንዲሁም በተቃራኒ ፆታዎች ስለፍቅርና ገጠመኞችን አስመልክቶ በግልፅ የሚወያዩበትና የሚዝናኑበት የፕሮግራም አይነት በመሆኑ መጠናት አለበት የሚል ጥያቄ በአዕምሮዬ በመፈጠሩ እንዳጠናው አነሳስቶኛል::

**1.2. የጥናቱ ዳራ**

የአማራ ብሄራዊ ክልል ድምፅ ከሚያስተላልፍቸው ፕሮግራሞች አንዱ በየሳምንቱ እሁድ ማታ ከ12:00-1:00 ሰአት የ"ሀሳብ ለሀሳብ" በሚል መጠሪያ የሚታወቀው በአማርኛ ቋንቋ የሚሰራጨው የመዝናኛ ፕሮግራም ነው:: ከክልሎች የመጀመሪያ የሆነው የአማራ ብሄራዊ ክልል ድምፅ በሚል ስያሜ በግንቦት 16/1989 ዓ.ም ዘወትር ከሰአት ከቅዳሜ እስከ እሁድ ከ11:00-2:00 ሰዓት እና ጠዋት ደግሞ ከ12:00-3:00 ሰዓት ፕሮግራሙን ያሰራጫል::

የራዲዮ ጣቢያው በኮምፒውተርና በዘመናዊ ዲጅታል መሳሪያዎች ተደራጅቶ በራሱ የመቅረጫ ስቱዲዮ ፕሮራሞችን ዘወትር ከምሽቱ 1:00-2:00 ሰዓት በኢትዮጵያ ሬዲዮ ማሰራጫ አማካኝነት ሲያስተላልፍ ቆይቷል:: ፕሮግራሙ እንዲቋቋም ከፍተኛ ትኩረት በመስጠትና አስፈላጊውን ሁሉ ጥረትና እገዛ በማድረግ በኩል የክልሉ መንግስት በዋነኝነት የሚጠቀስ ነው:: የስዊድን አለም አቀፍ ልማት ድርጅትም በገንዘብ፣ በሙያና በቴክኒክ ድጋፍ ያበረከተው አስዋጽኦ ትልቅ ግምት የሚሰጠው እንደሆነ በተደረገው ቃለ መጠይቅ ምልልስ የራዲዮ ጣቢያው ዳሬክተር አቶ ደረጀ ሞገስ ገልፀዋል::

በተጨማሪም በአሁኑ ጊዜ የፕሮግራም ክፍሉ 216 የሚደርሱ ሰራተኞች አሉት:: ፕሮግራሙም በአራት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ይሰራጫል:: በአማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ህምጠኛና አዊኛ ይተላለፋል:: የኦሮምኛ ፕሮግራሙ በክልሉ ለሚገኙትና በኦሮሞ ክልል ለሚገኙት ይሰራጭ ነበር:: በአሁኑ ጊዜ ግን በ2001 ዓ.ም ጀምሮ ብዙ አድማጭ ባለመኖሩ የተቋረጠ ሲሆን፤ በአዊኛም ፕሮግራሙ በምዕራብ ጎጃም ለሚኖሩ ለክልሉ ህዝቦች ይሰራጫል:: በህምጠኛ ቋንቋም በሰሜን ጎንደር ለሚገኙት የቅማንትኛ ቋንቋን ለሚናገሩ ህዝቦች ፕሮግራሙ ይሰራጫል::

እንዲሁም ፕሮግራሙ ሶስት ነገሮችን አቀናጅቶ በቴሌቪዥን እንደሚያስተላልፍ በራዲዮ እንደሚያሰራጭና የህትመት ስራውንም እንደሚሰራ የራዲዮ ጣቢያው ዳሬክተር ገልፀዋል:: ፕሮግራሙ ከሀገር ውስጥ እስከዚህ ድረስ ይደመጣል ብሎ ለመናገር ያስቸግራል:: ምክንያቱም

ጥራቱን ማወቅ ስለሚያስቸግር ነው:: ከሀገር ውጭም እስከ ሳውዲ አረቢያና እስከ ሶማሊያ፣ ሱዳንን ጨምሮ በጥራት ይደመጣል::

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍም በዚሁ በ"ሀሳብ ለሀሳብ" የሬዲዮ ፕሮግራም በተላለፉ የመዝናኛ ፕሮግራሞች ላይ ያተኩራል::

## 1.3. የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአማራ ብሄራዊ ክልል ድምፅ በ"ሀሳብ ለሀሳብ" የመዝናኛ ፕሮግራም ከጥቅምት 1 ቀን 2001 እስከ የካቲት 20 ቀን 2001 ዓ.ም የተላለፉትን የመዝናኛ ፕሮግራሞች መሰረት ያደረገ ነው:: በዚህ መሰረት የጥናቱ ዋና አላማዎች የሚከተሉት ናቸው::

ሀ. በራዲዮ ጣቢያው የተላለፉትን የፍቅር ግጥሞች፣ ቀልዶች፣ የአድማጮች ደብዳቤ፣ የፍቅር አባባሎችን መሰብሰብና ቅርፃቸውንና ይዘታቸውን መመርመርና መተንተን ነው::

ለ. በራዲዮ የመዝናኛ ፕሮግራም የተላለፉትን የፍቅር ግጥሞች፣ ቀልዶች፣ የአድማጮች ደብዳቤና የፍቅር አባባሎችን አንዴ በራዲዮ ከተላለፉፊ በኋላ ሁለተኛ ስለማይደገሙ እንደገና ማዳመጥና መመርመር ስለማይቻል ለመዝናኛነት የቀረቡትን ወደ ኋላ መለስ ብሎ ማየቱ ይጠቅም ዘንድ በወረቀት ላይ አስፍሮ በቅርስነት ለማስቀመጥ ነው::

ሐ. በራዲዮ ለመዝናኛ ፕሮግራም መቅረብ አለባቸው ብለው የሚፅሁፍትን የፕሮግራሙ ተሳታፊዎችን የችሎታቸውን ጥንካሬና ድክመት ምን እንደሚመስል ለመመርመር ነው:: በተጨማሪም በአብዛኛው የጥናት ወረቀቶች የተሰሩት በጋዜጣ ላይ በወጡ ግጥሞችና በታተሙ መፅሄቶች ላይ ነው:: ነገር ግን በራዲዮ የሚሰሙት የመዝናኛ ፕሮግራሞች ምን ጉድለት እንዳለባቸውና ጥንካሬያቸውንም ምን እንደሚመስል በጥናት ማሳወቁ በጣም ጠቃሚ ስለሆነ አጥኚው ትኩረት ሰጥቶ ከእነዚህ እውነታዎች ጋር በመነሳት ይህንን ጥናት በማጥናት ተዳሰዋል::

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

በራዲዮ የመዝናኛ ፕሮግራም ላይ በፍቅር ግጥሞች፣ ቀልዶች፣ የፍቅር አባባሎችና ደብዳቤዎችን በተመለከተ አድማጮች ስሜታቸውን በነፃነት በመግለፅ የሚዝናኑበት በመሆኑ እና የመዝናኛውን ፕሮግራም ለመረዳት የሚኖራቸው ፋይዳ ቀላል አይደለም:: ስለዚህ መጠናቱ በብዙ መልኩ አስፈላጊ ነው::

እነዚህን በራዲዮ ፕሮግራም በቀረቡት ነጥቦች መዝናኛን እንዴት መጠቀም እንችላለን ብለን ስንጠይቅ ጠቀሜታው የጎላ ነው:: በመዝናኛ ፕሮግራም የተላለፉትን የፍቅር ግጥሞችና

ቀልዶች እንዲሁም ደብዳቤን ሰብስቦ ማጥናቱ የሚከተሉትን ሶስት መሰረታዊ ፋይዳዎች አሉት::

1. በራዲዮ ላይ የመዝናኛ ፕሮግራም አድማጮች ስሜታቸውን በነፃነት የሚገልጹቸው ስለሆኑ፤ አሁን ያለውን የመዝናኛ ፕሮግራም ለመረዳት ስለሚያስችሉ ጠቃሚውን ሀሳብ ይበልጥ ለማዳበር ይጠቅማል::
2. እነዚህ ለመዝናኛ ፕሮግራም ይሆናሉ ተብለው የተላለፉትን ተሰብስበው ከተቀረፁ በኋላ ለሚመጣው ትውልድ እንዲህ ነበር ብሎ ለማሳወቅ ይጠቅማል:: በመቀጠልም ምን አይነት የመዝናኛ ፕሮችራም እደቀረቡ እና ቅርፃቸውና ይዘታቸወን ለማስረዳት ቁልፍ ሚና አላቸው::
3. በራዲዮ የመዝናኛ ፕሮግራም ላይ ጥልቅ ጥናት ለሚያደርጉ አጥኚዎች እንደመነሻ መረጃ በመሆን ይረዳል::

## 1.5. የጥናቱ ገደብ

በአማራ ብሄራዊ ክልል ድምፅ የመዝናኛ ፕሮግራሞች በአራት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች የሚተላለፍ ቢሆንም ለጥናቱ የተመረጠው ግን በአማርኛ ቋንቋ የሚተላለፈው የ“ሀሳብ ለሀሳብ” የመዝናኛ ፕሮግራም ብቻ ነው:: ጥናቱ በተለያዩ ቀናት በዜናና ወቅታዊ ፕሮግራሞች የቀረቡትን የመዝናኛ ፕሮግራሞች ሁሉ አያካትትም::

ጥናቱ ያተኮረበት የጊዜ ገደብ ከጥቅምት 1 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 15 ቀን 2001 ዓ.ም ድረስ ያለውን ብቻ ነው:: ይህ የሆነበት ምክንያትም ፕሮግራሙ በ1989 ዓ.ም የተጀመረ ቢሆንም፤ ሬዲዮ ጣቢያው የሚያስተላልፋቸውን ፕሮግራሞች መረጃ የማስቀመጥ ልምድ የለውም:: በመሆኑም ቀደም ብለው የተሰራጩትን ፕሮግራሞች ለመዳሰስ አልተቻለም:: ስለዚህ በ“ሀሳብ ለሀሳብ” የመዝናኛ ፕሮግራሞች የተላለፉትን መሰረት በማድረግ መረጃዎችን በተጠናከረ መልኩ በመሰብሰብ ከጥቅምት እስከ የካቲት ያለውን ጊዜ ያተኮረ ነው::

እንዲሁም ከጥቅምት 1 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 15 ቀን 2001 ዓ.ም የተላለፉትን ሁሉንም መተንተን ይቻል ነበር:: ነገር ግን ከጊዜ እጥረት፣ ከፕሮግራም መብዛት ከኢኮኖሚ አንፃር ሁሉንም ለመተንተን ስለማይቻል የተወሰኑትን በመምረጥ በፕሮግራሙ የተላለፉትን ከቅርፅና ከይዘት አኳያ ትንታኔ ተደርጎባቸዋል::

## 1.6. የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱን ለማካሄድ አጥኚው የመረጣታቸው መንገዶች ሶስት ናቸው:: የመጀመሪያው መንገድ በተለያዩ ቤተመጽሀፍትና ተዛማጅ ጥናቶችን በማንበብ ነው:: ሁለተኛው መንገድም የራዲዮ አዘጋጆችን ቃለመጠይቅ በማድረግ ነው:: ሶስተኛው መንገድ በራዲዮ ጣቢያው ድምፅ ላይብራሪ በመግባትና በማዳመጥ ነው:: እንዲሁም በ“ሀሳብ ለሀሳብ” የራዲዮ የመዝናኛ ፕሮግራም ከተላለፉት ውስጥ በፍቅር ግጥሞች፣ በፍቅር አባባሎች፣ ሙዚቃንና ደብዳቤዎችን አስመልክቶ 20 ያህሉን በመውሰድ ይዘታቸውንና ቅርፃቸውን በማየት ትንታኔ በማድረግ ተፈትሿል::

## 1.7. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ አጥኚው ሲያጠና ብዙ ችግሮች አጋጥመውት ነበር:: ከእነዚህም ችግሮች መካከል የመጀመሪያው ችግር ራዲዮ ጣቢያው እሩቅ ከመሆኑ የተነሳ መረጃ ለመሰብሰብ የገንዘብ ችግር ገጥሞት ስለነበር በሂደት እንዲፈታ አድርጓል:: ለራዲዮ ጣቢያው ዳይሬክተር ለአቶ ደረጀ ሞገስ በቀረበላቸው ቃለ ምልልስ መሰረት ኮፒ ማድረግ አይቻልም በማለታቸው በራዲዮ ጣቢያው የድምፅ ላይብራሪ በመጠቀም እየመላለሱ ማዳመጥና መፃፍ ትልቅ ችግር ነበር:: ነገር ግን በሂደት ችግሩ እንዲፈታ ተደርጓል::

በመቀጠልም ይህን የኮፒ ስራ ለማስኬድ ስላልተቻለ ለማቃለል ጓደኞቼን በመወከል በፖስታና በመኪና እየተላኩ እንዲመጡ በመደረጋቸው ችግሮች በሂደት ተፈትተዋል:: ሌላው በሙዚቃ ፕሮግራም የቀረቡትን መዝናኛዎች ከይዘትና ከቅርፅ አንፃር ለመተንተን የሙዚቃ ግጥሞችን ለማግኘት በጣም ከባድ ነበር:: ነገር ግን ከሙዚቃ ቤቶች በመሄድና በመጠየቅ ችግሮች እንዲፈቱ ሆነዋል:: እንዲሁም ለጥናቱ አጋዥ መፅሀፍት በራዲዮ ላይ የሚያነሱ መጽሀፎችን በበለጠ ለማግኘት አቡነጴጥሮስ በሚገኘው የጆርናሊዝም ቤተመጽሀፍት በመሄድና በመጠቀም ችግሩ እንዲቃለል አጥኚው ጥረት አድርጓል::

ከዚህ በመቀጠልም ጥናቱን ለማካሄድ የራዲዮ ጣቢያ እሩቅ ከመሆኑ የተነሳ የስልክ ችግርና መረጃውን ከዋናው ፖስታ ለመቀበል የገንዘብና የጉልበት ችግር ነበር:: ነገር ግን እነዚህን ችግሮች አጥኚው ሳይሰለች በቀላሉ በመፍታት ጥናቱን እንዲያጠናቅቅ ሆኗል::

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ክለሳ ድርሳን

### 2.1. የመዝናኛ ምንነት

መዝናኛ የሚለው የአማርኛ ቃል ብዙ ሀሳቦችን የሚገልፅ ነው:: መዝናኛ ልዩ ጉዳዮችን ይጠቅሳል:: ኳስ ጨዋታን መመልከት፣ ከዘመድ ጋር መጫወት፣ ቼዝ መጫወት፣ ዳማ መጫወት ወዘተ … የሚሉት ሁሉ መዝናኛ በሚለው ቃል ስር የሚጠቃለሉ ናቸው:: ይህን ሀሳብ አስመልክቶ /ከሳቴ ብርሃን 1951፣1336/የሚከተለውን ብለዋል::

መዝናኛ ተዛና ተማመነ፣ እንደልቡ

ያለሀሳብ ሆነ፣ ተዛለነ፣ ይሉኝ ማለት ነው::

ለቃሉ የተሰጠው ብያኔ ሰዎች ሲዝናኑ ሰው ምን ይለኝ ሳይሉ በነፃነት ይዝናናሉ:: በተጨማሪም በእረፍት ጊዜያቸው ከሀሳብ ነፃ ሆነው እንደሚዝናኑና እንደሚደሰቱ በግልፅ ትንታኔ ሰጥተውት ይገኛሉ:: ይሁን እንጂ የመዝናናት ምንነት ከዚህ የሰፋ ነው:: /ማርቲንሄነሪ፣ 1892፣17/ የሚከተለውን አቅርበዋል::

*መዝናኛ በእረፍት ጊዜ በግልም ሆነ በቡድን የሚከናወን አላማ ያለው ነፃ የሆነ የሚያስደስት ማንኛውም ድርጊት ነው:: በውስጡም ልዩ ልዩ ጨዋታዎችን፣ ስፖርትን፣ እሩጫን፣ ቀልዶችን፣ ሰንክንንና የፈጠራ ስራን ይይዛል::*

ከላይ የተገለፀው ሀሳብ ሰዎች በግልም ሆነ በቡድን ለአላማ ብለው የሚያደርጉት ልዩ ልዩ የጨዋታ አይነት መዝናኛ መሆኑን ያስረዳል:: እንዲሁም ሰዎች በእረፍት ጊዜአቸው እራሳቸውን ለማስደሰት ሲሉ የሚፈፅሙት የጨዋታ ድርጊት መዝናኛ መሆኑን ይገልፃል:: ከዚህ በመቀጠልም /አለንቢክተር 1961፣1271/ የሚከተለውን አቅርበዋል::

*መዝናኛ በርከት ያሉ ጉዳዮችን የሚያጠቃልል ሲሆን እድሜንና ፆታን ሳይለይ ማንኛውም ሰው በድርጊት ወይም በተመልካችነት የሚካፈልበት ማንኛውም የእረፍት ጊዜ እንቅስቃሴ ነው:: በዚህም መልኩ የጨዋታን ብያኔ በውስጡ ሲያቅፍ በተጨማሪም የህብረተሰቡን ግንኙነትና ሙያንም ይገልፃል::*

ከላይ የቀረበው ሀሳብ መዝናኛን ከጨዋታ ይልቅ በርከት ያሉ ድርጊቶችን የሚያካትት የጨዋታን ብያኔ በውስጡ የያዘ፤ በእረፍት ጊዜ የሚከናወኑትን ድርጊቶችንና የፈጠራ ስራዎችን ጭምር የሚያጠቃልል፣ ከግል ይልቅ ማህበራዊነትን የሚመለከት ማለት ይቻላል::

## 2.2. የራዲዮ መዝናኛ ፕሮግራም ምንነት

የሬዲዮ መዝናኛ ፕሮግራም ምንነት የሚያወሳ እራሱን የቻለ የመረጃ ምንጭ ለማግኘት በመገናኛ ብዙሃን ከሚሰሩ ስራዎች ጋር አዛምዶ በማየት ስለምንነቱ ለመናገር ይቻላል:: የራዲዮ መዝናኛ ፕሮግራም በራዲዮ ቀልዶችን፣ መልዕክቶችን፣ ግጥሞችንና ደብዳቤዎችን በማስተላለፍ ሰዎችን ለማስደሰት ይሞክራል::

የራዲዮ መዝናኛ ፕሮግራም አቅራቢዎች የራዲዮውን ግብአተ ድምፅ አጠቃቀም ለአድማጮች በሚመች ሁኔታ ካልቀረበ የመዝናኛው ፕሮግራም ሳቢነት አይኖረም:: እንዲሁም በመሀሉ ጣልቃ የሚገቡት ሙዚቃዎች ከሚያነሷቸው ርእሰ ጉዳዮች ጋር ተያያዥነት ያላቸውና የአድማጮችን ስሜት የሚጠብቁ መሆን አለባቸው:: ይህ ከሆነ አዝናኝነታቸው የጎላ መሆኑ አያጠራጥርም:: የራዲዮ መዝናኛ ፕሮግራም ምንነት ከሚጠቁሙ መፅሀፎች ውስጥ አንዱ /ባክስ 1979፣35/ የሚከተለውን ገልጿል::

> *መዝናኛ ማለት የህዝብን የማዳመጥ ስሜት በተቻለ መጠን ለመቆደጣጠር የሚያገለግል ፕሮግራም ነው:: የመዝናኛው ፕሮግራም አላማም የሰዎችን ፍላጎት በማርካት ማዝናናት ነው:: ነገር ግን የሬዲዮን ፕሮግራም ማድመጥ ወይም መከታተል አስቸጋሪ ነው:: የሬዲዮ የመዝናኛ ፕሮግራም ሊሳካ የሚችለው አድማጮች ከብዙሃን መገናኛ ጋር ሲግባቡ ወይም በትኩረት መከታተል ሲችሉ ነው::*

ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው በሬዲዮ የመዝናኛ ፕሮግራም በሚተላለፍበት ጊዜ የብዙሃኑን ስሜት ታሳቢ በማድረግ ለማዝናናት የሚያገለግል ነው:: የመዝናኛው ፕሮግራም አላማም የአድማጮችን ፍላጎት መሰረት በማድረግ እያዝናና ማቅረብ ነው:: በተጨማሪም /ማክሊሽ፣ 1999፣9/ የሚከተለውን አቅርበዋል::

> *ሰዎች ችግር በሚገጥማቸው ጊዜ ብቻቸውን ሬዲዮ በማድመጥ ይዝናናሉ:: የመዝናኛውን ፕሮግራም በሚያዳምጡበት ጊዜ የታሪኩን ፍፃሜ ምን ይሆን በማለት በመጓጓትና በመጨረሻም የታሪኩን ፍፃሜ በመስማት የመንፈስ እርካታን በማግኘት ይዝናናሉ:: በተጨማሪም ሰዎች ብቻቸውን በሚሆኑበት ጊዜ ስሜታቸው በሚቀነስበት ጊዜ ከጓደኛ ጋር በመሆን ሬዲዮ በማድመጥ ይዝናናሉ::*

ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው ሰዎች ችግር በሚገጥማቸው ጊዜ ብቻቸውን የሬዲዮ ትረካ በማድመጥ ይዝናናሉ:: የሬዲዮን ትረካ በሚያዳምጡበት ጊዜ የመዝናኛው ትረካ አሁን ምን

ይሆን? በመጨረሻውስ ምን ይሆን? እያሉ ለመስማት ያላቸው ጉጉት ከፍተኛ እንደሆነ እና ሰዎች ብቻቸውን በሚሆኑበት ጊዜ የመንፈስ መረበሽ ስለሚያጋጥማቸው ከጓደኛ ጋር በመሆን እንደሚዝናኑ ያስገነዝባል:: ስለዚህ ሰዎች ሬዲዮ በሚያዳምጡበት ጊዜ ብቻቸውንና ከጓደኛ ጋር በመሆን የሬዲዮ ትረካ በማዳመጥ እንደሚዝናኑ ይጠቁማል::

በአጠቃላይ የራዲዮ መዝናኛ ፕሮግራሞች አቀራረቦች አራት ናቸው:: እነሱም ሙዚቃ፣ ውይይት ደብዳቤና ግጥሞች መሆናቸውን የራዲዮ መዝናኛ ሀላፊ አቶ መልኬ ከበደ በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ መሰረት ገልፀዋል:: ስለዚህ የአማራ ብሄራዊ ክልል መደበኛ የራዲዮ ድምጽ የ“ሀሰብ ለሀሳብ” ፕሮግራም አቀራረብ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው::

### 2.2.1. ሙዚቃ

ሙዚቃ ሰዎች መሳሪያ በመጠቀም በድምፅ አማካይነት የሚዘፍኑት የመዝናኛ አይነት ነው:: ሙዚቃ የሁሉም ቋንቋ ናት:: ለዚህም ነው አንዳንድ ሰዎች ሙዚቃ ህይወት ናት የሚሉ:: ሙዚቃ ሲሰማ መንፈሱ የማይደሰት ሰው አለ ለማለት ያስቸግራል:: የሙዚቃው ምርጫው ግን እንደየግለሰቡ ሊለያይ ይችላል:: የተወሰነው የድምጽ ምቱ ፈጣን የሆነ ሲወድ ሌላው ግን ለስለስ ያለናዝግ ብሎ የሚለቀቀውን ዜማ ይወዳል:: የፊቱን በማስታወስ እንደየ ፍቅር ትዝታና ወኔን የሚቀሰቅሱ ሙዚቃዎችን የሚያዳምጡ የተለያዩ ግለሰቦች ናቸው::

ሙዚቃ በበርካታ የጥበብ ቀማሪዎች ተመርጦ የሚዘጋጅ ነው:: ድምጻዊው፤ በግጥም፤ በዜማ፣ ደራሲዎች እነዚህ በሙዚቃ መሳሪያ በመታገዝ ተጨዎቾች በህብረት ተጠንቅቀው ድምፃቸውን ለአድማጮች ጆሮ የሚያሰሙበት መንገድ ነው:: ሙዚቃ በሁለት አይነት መንገድ ይዘጋጃል:: አንደኛው ዘመናዊ ሙዚቃ ነው:: ይህ የሙዚቃ አይነት በዘመናዊ መሳሪያ በመታገዝ በአብዛኛው የተቃራኒ ፍቅረኞችን በተመለከተ በሚስብ መልክ የሚቀርብበት ነው::

ሁለተኛው ደግሞ ባህላዊ ሙዚቃ ነው:: ማንኛውም ሰው የራሱ የሆነ ቋንቋ፣ ወግ፣ ልምድ፣ ሀይማኖት አለው:: በመሆኑም ሙዚቃ ባህል ይንፀባረቅበታል:: ስለዚህ ባህልን በተመለከተ ሙዚቃ በማዘጋጀት ባህሉን ተወዳጅና ሙዚቃውም እንዲደመጥ ያደርገዋል:: የሙዚቃ ምንነት /በአዳምስ፣ 1999፣180/ ከዚህ በታች እንዲህ ይገልፀዋል::

> *ሙዚቃ ለማህበረሰቡ በጣም ጠቃሚ ነው:: ምክንያቱም ባህልና ፈጠራ ይንፀባረቅበታል:: የሙዚቃ አቀራረብም ይለያያል:: የሚለይበትም የአድማጮች ፍላጎት ሁልጊዜ አንድ ስለማይሆን ነው:: አዲስ ሙዚቃ ለአድማጮች ትኩረት*

*ሰጥቶ በሚቀርብበት ጊዜ የደበዘዘውን የሰው ልጅ ስሜት በማነቃቃት እንዲዝናኑ ያደርጋል::*

የዚህ ጥቅስ አባባል እንደሚያስረዳው ሙዚቃ ለማህበረሰቡ ጠቃሚ ነው:: ምክንያቱም ባህልና የፈጠራ ስራ ስለሚንፀባረቅበት ነው:: በተጨማሪም የሙዚቃ ምርጫ እንደየሰዎች ፍላጎት ይለያያል:: እንዲሁም ሙዚቃ ለአድማጮች ጆሮ በሚደርስበት ጊዜ እንዲነቃቁና ዘና እንዲሉ ያደርጋል::

### 2.2.2. ውይይት

ውይይት አንድና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚደረግ ምክክር ነው:: ውይይቱም በሀገር ጉዳይ የቢሮስራን፣ እንዲሁም የወደፊት የስራ እቅድን አስመልክቶ በመመካከር የሚደረግ ሂደት ነው::

በራዲዮ ከሚቀርቡት የፕሮግራም አይነቶች አንዱ ውይይት ነው:: የውይይት ፕሮግራም በወጣቶችና በታላላቅ ሰዎች መካከል የሚደረግ ነው:: የውይይት ምንነነት /በጂም 1957፣17/ በሰፊው እንደሚከተለው አቅርቦታል::

*ለራዲዮ አዘጋጆች አንድ የተለየ መንገድ ነው የሚባለው የውይይት ፕሮግራም ነው:: ውይይት ማንኛውንም ሁኔታ የሚብራራበት፣ የትኛውም አወዛጋቢ የሆነ መረጃ የሚብራራበት ነው::*

የዚህ ጥቅስ አባባል በሬዲዮ የውይይት ፕሮግራም ከሌሎች ፕሮግራሞት የለየ ሆኖ የሚቀርብ ነው:: ምክንያቱም ማንኛውም አወዛጋቢ የሆኑ ችግሮች የሚብራሩበትና ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች የሚቀርቡበት በመሆኑ በተለየ መልኩ ግንዛቤን በማስጨበጥ ገልፆታል::

የ"ሀሳብ ለሀሳብ" የራዲዮ ፕሮግራም በወጣቶች ዙሪያ ስለተቃራኒ ፍቅር እንዲሁም በታላቅ ሰዎች ደግሞ ከህይወት ተሞክሮአቸው አኳያ ከ10-15 ደቂቃ ውይይት ያደረጋል:: ውይይቱ በሚካሄድበት ጊዜ አድማጮችና የስልክ ተሳታፊዎች እንዳይሰለቹ በመሀል ለአምስት ደቂቃ ያህል ሙዚቃን በመጠቀም አድማጮችንና የስልክ ተሳታፊዎችን እንዲዝናኑ ያደርጋል::

### 2.2.3. ደብዳቤ

የሰው ልጅ ሀሳቡን በፅሁፍ በማስፈር ለጓደኛው ለቤተሰብ እንዲሁም ለዘመድ በደብዳቤ በመፃፍ መልዕክቱን ያደርሳል:: ደብዳቤ ሲፃፍ እንደሰዎች ቅርበትና ርቀት ይለያያል:: ለምሳሌ ለፍቅረኛ የሚፃፍ ደብዳቤ ከሆነ፤ ምን ያህል ሀሳቤን በደብዳቤው ላይ ይገልፅልኛል? ፍቅረኛዬን ምን ያህል ያሳምንልኛል? በማለት በተመረጡ ቃላትና ሀሳቦች በመጠቀም ይፃፋል:: እንዲሁም ለቤተሰብ የሚፃፍ ደብዳቤ የራሱ የሆነ ቅርፅ አለው:: ስለዚህ የደብዳቤ አፃፃፍ እንደሰዎች ቅርበትና ርቀት የሚወሰንና የሚፃፍ ነው::

የራዲዮ ፕሮግራም አድማጮች እንዲሁም የስልክና የፖስታ ተጠቃሚዎች ስለራሳቸው ችግር ለመፍታት ብሎም በማህበራዊ ችግሮች ስለተቃራኒ ፆታ በፍቅር ዙሪያ በደብዳቤ ሀሳባቸውን በመግለፅ ይዝናናሉ:: ይህን ሀሳብ አስመልክቶ /ግራፍት 1991:72/ ከዚህ በታች በግልፅ አቅርቦታል::

*አንዳንድ የሬዲዮ ደንበኞች ለሬዲዮ ዝግጅት ክፍል ደብዳቤ ይፅፋሉ:: የራዲዮ አዘጋጆችም የአድማጮችን ደብዳቤ ለሌሎች አድማጮች ማነቃቂያ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን መረዳት አለባቸው:: ነገር ግን በደብዳቤ የትረካ ጊዜ ሁሉንም ደብዳቤዎች አያካትትም:: አንድ ወይም ሁለት የአድማጮች ደብዳቤ ብቻ በዝግጅቱ ላይ በሚያዝናና ሁኔታ ይቀርባል::*

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው አንዳንድ የሬዲዮ ደንበኞች በስልክና በደብዳቤ መፃፍና ማንበብ የሚችሉ ለራዲዮ ዝግጅት ክፍል ደብዳቤ እንደሚፅፍና ተሳትፏቸውም እንደሚበረታታና እንደሚዝናኑ ያስረዳል:: በተጨማሪም የሬዲዮ አዘጋጆች የአድማጮችን ደብዳቤ በትረካ መልክ በማንበብ ያቀርባሉ:: ከደብዳቤዎች መብዛት የተነሳ ጥቂቶች ደብዳቤዎችን ብቻ እንደሚቀርቡ ይገልፃል::

### 2.2.4. ግጥም

ግጥም የሰው ልጅ እምቅ የሆነ የውስጥ ስሜቱን ሀዘኑንና ደስታውን ጥላቻውንና ፍቅሩን በቋንቋ የሚገልፅበት ነው:: በአንድ ቃል ብዙ ነገር ለመግለፅ የሚያስችል የፈጠራ ስራ ነው:: ከ“ሀሳብ ለሀሳብ” የራዲዮ ፕሮግራምም ደንበኞች ሀሳባቸውን በግጥም የሚያንፀባርቁበት ነው:: ግጥም ጊዜን በመቆጠብ በአጭርና በተወሰኑ ቃላቶች በመጠቀም የፈለጉትን ሀሳብ

ለመግለፅ የሚያስችል አንዱ የስነ ፅሁፍ ዘርፍ ነው:: የግጥምን ብያኔ አስመልክቶ /ዘሪሁን አስፋው፣ 1996፣73/ አቅርበውታል::

*ስነ ግጥም በእጅጉ ጥንታዊነት እንዳለው የሚነገርለት የኪነጥበብ ዘር ነው:: የሰው ልጆች ለብዙ ዘመናት ደስታና ሀዘናቸውን፣ ምኞት ፍላጎታቸውን፣ የአኗኗር ሁነታቸውንና ልዩ ልዩ ገጠመኞቻቸውን በማንጎራጎርና በማዜም ሲገልፁበተ ኖረዋል:: ስነ ግጥም በጣም ምርጥና ደስተኛ ከሆኑ አዕምሮዎች የፈለቁ ምርጥና አስደሳች የሆኑ አጋጣሚዎች ዘገባ ነው:: ስለዚህ በአለም ውስጥ ውብና የተሻለ ነው የሚባለውን ሁሉ ህያው ያደርገዋል::*

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው የስነግጥም ምንነት በሰፊው ተገልጿል:: ስነ ግጥም የሰው ልጆች ደስታቸውንና ምኞታቸውን እንዲሁም ገጠመኞቻቸውን አስመልክቶ የውስጥ ፍላጎታቸውን በግጥም በመግለፅ የሚዝናኑበት ነው:: ከዚህ በታች በሚቀርበው /በዓለማየሁ ሞገስ፣ 1954፣5/ እንደሚከተለው ቀርቧል::

*ማንኛውም ዝርው ቤት እየመታ በስንኝ ተሳክቶ ሲነገር ግጥም ይባላል:: ይህም ቤት እየመቱ የመፅሀፍ ዘዴ እንጂ የንግግር ስልት አይደለም::*

ከላይ የቀረበውን የግጥም ብያኔ ስንመለከት ማንኛውም ዝርው የሆነ ቤት የሚመታ እና በስንኝ ተደራጅቶ ሲቀርብ ግጥም እንደሚፈጥር በሰፊው አብራርተዋል:: እንዲሁም ግጥም ሲፃፍ ቤት እንዲመታ ተደርጎ በስንኝ ተከፍሎ እንደሚፃፍ ያስረዳሉ:: በተጨማሪም የፅሁፍ ስልት እንጅ የንግግር ስልት እንዳልሆነ በጥልቅ ያስገነዝባሉ::

የ"ሀሳብ ለሀሳብ" የራዲዮ ፕሮግራም የሰዎችን ትኩረት ለመሳብና ፍላጎታቸውን ለማርካት ሲፈለግ አራቱን የመዝናኛ ፕሮግራም በሙዚቃ፣ በውይይት፣ በደብሳቤና በግጥም በመጠቀም አድማጮች እንዲዝናኑ ያደርጋል:: በራዲዮ ንግግር በሚደረግበት ጊዜ አድማጮች እንዳይሰለቹ በመሀል ሙዚቃ በመጠቀም ፕሮራሙን በማስተላለፍ አድማጮችን ያዝናናል:: እንዲሁም ባህላዊና ዘመናዊ ሙዚቃ በመምረጥ ወጣቶችንና አዋቂዎችን በማገናዘብ ያስደስታሉ::

ሌላው በራዲዮ የውይይት ፕሮግራም አድማጮች በአንድ አስፈላጊ ጉዳይ ላይ በሚወያዩበት ጊዜ በመሀል ሙዚቃና ቀልድ በመጠቀም በሚስብ መልክ ይቀረባል:: ከገጠመኝ

አንፃር ግለሰቦች የራሳቸውን ታሪክ በመግለፅ በሚስብ ሁኔታ ይቀርባል:: በተጨማሪም አድማጮች የላኩትን ደብዳቤ እንዲደርስና እንዲቀርብ በማድረግ ያስተላልፋሉ::

በአጠቃላይ ከላይ የተገለፁትን አራት አይነት ፕሮግራሞችን ከግምት በማስገባት አድማጮችን እንዲዝናኑ ያደርጋል:: በግጥም ፕሮግራም ጊዜ አድማጮች ስሜታቸውን ተቆጣጥረው ግጥማቸውን በመፃፍ ለአድማጮች በማድረስ ራሳቸውንና የሌሎችን አድማጮች እንዲዝናኑ ያደርጋል::

## 2.3. የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ክፍለ ትምህርት ውስጥ ከቀረቡት ዲማጾቸ መካከል ከእኔ ጥናት ጋር በቀጥታ የሚዛመድ ስራ አልተገኘም:: ይሁን እንጂ በአጠቃላይ በሬዲዮ በተላለፉ ግጥሞች ላይ አቀራረባቸው ቢለያይም አራት ዲማጾች ቀርበዋል:: ከጥናቱ ጋር ዝምድና ያላቸው ጥናታዊ ፅሁፎች እንደሚከተለው ተከልሰዋል:: ከእኔ ጥናት ጋር የሚዛመዱ ከአራቱ ዲማጾች ከዚህ በታች ቀርበዋል::

በመጀመሪያ ይልማ ጥበቡ በ1976 ዓ.ም "በአብዮታዊት ኢትዮጵያ ድምፅ የተላለፉ የአማርኛ ውዳሴ በአላት መዝሙሮችና ዘፈኖች" በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ ነው:: ይልማ ጥናቱን በአራት ምዕራፎች ከፋፍሎ አጥንቷል:: ይልማ ዋና አላማ ያደረገው የመዝሙሮችንና የዘፈኖችን እንዲሁም የግጥሞችን ባህሪያትና የሚታዩባቸውን ጉድለትና ጥንካሬ ከይዘት አኳያ ተንትኗል:: የእኔ ጥናታዊ ፅሁፍም ዋና አላማ አድርጎ የተነሳው በራዲዮ ጣቢያው የተላለፉትን የፍቅር ግጥሞች፣ ቀልዶች፣ ደብዳቤዎችና የፍቅር አባባሎችን በመሰብሰብና ቅርፃቸውንና ይዘታቸውን ለመመርመርና ለመተንተን ነው:: አላማውንም የግጥሞቹን ባህሪያቶች በመተንተን አሳክቷል::

የይልማ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሁለታችንም በራዲዮ በተላለፉ ግጥሞች ላይ የይዘት ትንተና በማድረጋችን ነው:: ይሁን እንጂ የይልማ ጥናት ትኩረቱ መዝሙሮችና ዘፈኖች ላይ የተመሰረተ ሲሆን፤ የእኔ ጥናት ደግሞ የፍቅር ግጥሞች፣ ቀልዶች፣ ደብዳቤ፣ የፍቅር አባባሎችና ሙዚቃ ላይ ያተኮረ ነው:: ሌላው ተመሳስሎአችን የመዝናኛ ፕሮግራሞችን መቃኘታችን ላይ ነው:: ልዩነታችን ደግሞ የይልማ ጥናት በበአላት ላይ የእንቁጣጣሽ፣ የመስከረም ሁለት፣ የመጋቢት ሀያስምንት፣ የመዝሙሮችንና የግጥሞቹን ከይዘት ብቻ በመተንተን ሲነበቡና ሲዜሙ ያላቸውን ባህሪያት አሳይቷል:: የእኔ ጥናታዊ ፅሁፍ

ደግሞ የፍቅር ግጥሞች፣ ቀልዶች፣ ደብዳቤዎች፣ የፍቅር አባባሎችና ሙዚቃዎችን በመሰብሰብ ከቅርፅና ይዘት አንፃር ተተንትነዋል::

በሁለተኛ ደረጃ የምናየው አበዛ አባተ በ1988 ዓ.ም "በደብረማርቆስ ሬዲዮ በእሁድ የመዝናኛፕሮግራም የተላለፉ ግጥሞች" በሚል ርዕስ ያቀረበውን ጥናታዊ ጽሁፍ ነው:: አበዛ ጥናቱን በሶስት ምዕራፎች ከፋፍሎ አጥንቷል:: የጥናቱ አላማ አድርጎ የተነሳው ማህበራዊ ጉዳዮችን መሰረት አድርገው የተገጠሙትንና የስነፅሁፉ፣ የፈጠራ ስራ ችሎታን በማየት ትንታኔ በመስጠት ማወቅና ማስረዳት እንደሆነ ተገልጿል:: የእኔ ጥናታዊ ፅሁፍ ዋና አላማ አድርጎ የተነሳው በራዲዮ የመዝናኛ ፕሮግራም የተላለፉትን የፊቅር ግጥሞች፣ ቀልዶች፣ ደብዳቤዎች፣ የፍቅር አባሎችና ሙዚቃዎች አንዴ በራዲዮ ከተላለፉ በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ ስለማይደገሙ እንደገና ማዳመጥና መመርመር ስለማይቻል በወረቀት ላይ አስፍሮ በቅርስነት ማስቀመጡ የተሻለ ነው በሚል ነው::

የአበዛ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ጉዳይ ቢኖር ሁለታችንም በራዲዮ የመዝናኛ ፕሮግራም በቀረቡ የፍቅር ግጥሞች ላይ ጥናት ማካሄዳችን እና ጥናታችን በሬዲዮ በተላለፉት ፕሮግራሞች የቅርፅ ትንተና የሚዳስሱ በመሆናቸው ነው:: ልዩነታቸውም የአባዛ የይዘት ትንተናውን በጥሞች ላይ ያደረገ ሲሆን፤ የኢኮኖሚ ይዘት፣ የግጥሞችን ጭብጥ፣ ጎጅ ባህሎችንና ጠቃሚ ባህሎችን በአጠቃላይ የጎጃም ምድርን በተመለከተ የተገጠሙ በማለት የይዘታቸውን ትንታኔ አቅርቧል:: የእኔ ጥናታዊ ፅሁፍም በፍቅር ግጥሞች፣ ቀልዶች፣ በፍቅር አባባሎችና ሙዚቃዎች ላይ ከይዘትና ቅርፅ አኳያ ትንታኔ ማድረጉ ያለያያቸዋል::

በሶስተኛ ደረጃ የአበባው ዘውዴ በ1989 ዓ.ም "በሬዲዮፋና የመዝናኛ ፕሮግራም በቀረቡ ግጥሞች ከይዘታዊ ትንተና" አንጻር በሚል ጥናታዊ ጽሁፉን አቅርቧል:: የጥናቱ አላማ አድርጎ የተነሳው በሬዲዮ ፋና የመዝናኛ ፕሮግራም በተላለፍ ግጥሞች ይዘታዊ ትንታኔ ለማካሄድ ግጥሞቹ ምን ምን ጉዳዮችን እንደዳሰሱ መልዕክቶቻቸውን መመርመሩና ማብራራቱ ነው:: የእኔ ጥናታዊ ፅሁፍም ዋና አላማ አድርጎ የተነሳው በራዲዮ የሚሰሙት የመዝናኛ ፕሮገራሞች ምን ጉድለት እንዳለባቸውና ጥንካሬያቸው ምን እንደሚመስል በጥናት ማሳወቁ ጠቃሚ ስለሆነ ከእነዚህ እውነታዎች ጋር በመነሳት ከቅርፅና ይዘት አንፃር ትንታኔ ተደርጎባቸዋል::

የአበባውና የአኔ ጥናት የሚመሳሰሉበት በመዝናኛ ፕሮግራም በቀረቡ የፍቅር ግጥሞች ላይ በማትኮራቸው እና ግጥሞቹን ከይዘታቸው አኳያ መተንተናቸው ነው:: የአበባው ጥናት ስለኑሮ ስፖርት፣ ባህላዊና ኪነጥበብን በሚመለከት ይዘታቸውን በተመለከተ ጥናት ያደረገ ሲሆን፤ የእኔ ጥናትም በመዝናኛ ፕሮግራም በተላለፉ የራዲዮ ፕሮግራም በፍቅር ግጥሞች፣ ቀልዶች፣

ደብዳቤዎች፣ ሙዚቃዎችና በፍቅር አባባሎች ላይ የቅርፅና ይዘት ትነታኔ የተደረገባቸው ናቸው:: ስለዚህ የአበባው ጥናታዊ ፅሁፍ ይዘት ላይ ብቻ የተመለከተ ሲሆን የእኔ ጥናት ግን ይዘትንና ቅርፅን በሰፊው በማየት ልዩነታቸውን ለመመልከት ሞክሬአለሁ::

በአራተኛ ደረጃ በሪሁን ስመኝ በ1990 ዓ.ም በ"ደሴ ሬዲዮ ጣቢያ የመዝመናኛ ፕሮግራም የተላለፉ የውዳሴ በአላት ግጥሞች" የቅርፅ ትንተና በሚል ያቀረበውን ጥናት ነው::

በሪሁን ዋና አላማ አድርጎ የተነሳው በደሴ ሬዲዮ ጣቢያ የቀረቡትን የውዳሴ በአላት ግጥሞች ከስነ ግጥም ዓለባውያን አኳያ ትንተና በማድረግ ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን ለማሳየት ሞክሯል::

የእኔ ጥናት ዋና አላማ በራዲዮ ጣቢያው የተላለፉትን የፍቅረ ግጥሞች፣ ቀልዶቸ ደብዳበዎች፣ የፍቅር አባበሎችና ሙዚቃዎችን በመሰብሰብና ቅርፃቸውንና ይዘታቸውን መመርመርና መተንተን ነው::

የበሪሁን ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው፤ የበሪሁን ጥናት በደሴ ሬዲዮ ጣቢያ የመዝናኛ ፕሮግራም የውዳሴ በአላት ግጥሞችን ከቅርፅ ትንተና ያቀረበ ሲሆን፤ የእኔ ጥናታዊ ፅሁፍም በባህርዳር ከተማ በአማራ ብሄራዊ ክልል ድምፅ በተላለፉ የመዝናኛን ፕሮግራም ላይ በፍቅር ግጥሞች፣ ቀልድ፣ በደብዳቤ በፍቅር አባባሎችና ሙዚቃዎችን በተመለከተ ቅርፃቸውንና ይዘታቸውን በመተንተን ነው:: ስለዚህ ሁለታቸውም ቅርፅን የሚዳሰሱ በመሆናቸው ያመሳስላቸዋል:: እንዲሁም ሁለታቸውም በሬዲዮ የመዝናኛ ፕሮግራም ላይ መሰራታችን ሊያመሳስለን ችሏል::

ሌላው የሚያለያያቸው ጉዳይም አለ:: የበሪሁን ጥናት በመዝናኛ ሬዲዮ ፕሮግራም በተላለፉ የውዳሴ በአላት ግጥሞችን ከቅርፅ አንፃር ብቻ ትንታኔ ያደረገ ሲሆን፤ የእኔ ጥናት ደግሞ በመዝናኛ የራዲዮ ፕሮግራም በተላለፉ የፍቅር ግጥሞች፣ ደብዳቤዎች፣ የፍቅር አባባሎችና ሙዚቃዎች ላይ ከቅርፅና ይዘታቸው አኳያ በሰፊው ትንታኔ መደረጉ ሊያለያያቸው ችሏል:: ስለዚህ የበሪሁን ከቅርፅ ብቻ ነጥሎ ትንታኔ ያደረገ ሲሆን፤ የእኔ ጥናትም ቅርፅንና ይዘትን ጨምሮ መተንተኑ ልዩነት እንዳላቸው ያስገነዝባል:: ከአራቱ ዲማፆች ውስጥ በአማራ ብሄራዊ ክልል በመደበኛው የራዲዮ ድምፅ በተላለፍ የመዝናኛ ፕሮግራም የተደረገ ጥናት የለም::

በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩት ጥናታዊ ፅሁፎች ከኔ ጥናት ጋር ያላቸው ግንኙነት ሁሉም ጥናቶች በሬዲዮ የመዝናኛ ፕሮግራም ላይ በቀረቡ ግጥሞች ላይ ትንተና በማድረጋቸው ነው:: የሁሉንም ተከላሽ ጥናቶች ስንመለከትም የሬዲዮ መዝናኛ ግጥሞችን በፅሁፍ መልክ

ለተተኪው ትውልድ በቅርስነት ለማስቀመጥና የሬዲዮ ጣቢያዎችንም ለማስተዋወቅ ሞክረዋል:: በዚህ ረገድ ሲታይ የእኔም ተጨማሪ ነው ማለት ይቻላል::

በሌላ መልኩ ደግሞ ከላይ የተጠቀሱት ጥናቶች ከእኔ ጥናት ጋር የሚያለያያቸው መሰረታዊ ጉዳይ አለ:: ይኸውም የእኔ ጥናት የግጥሞቹን ቅርፅና ይዘት ዘርዘር አድርጎ ማቅረቡ ላይ ነው:: በተጨማሪም በራዲዮ የመዝናኛ ፕሮግራም በቀረቡ የፍቅር ግጥሞች፣ ሙዚቃዎች፣ ቀልዶችንና ደብዳቤችን የሚቃኝ ስለሆ ከዚህ በፊት ከተሰሩት ስራዎች የተለየ ሆኖ ቀርቧል::

## ምዕራፍ ሶስት

## 3. በ"ሀሳብ ለሀሳብ" በራዲዮ በተላለፉ የመዝናኛ ፕሮግራም የይዘት ትንተና

የ"ሀሳበ ለሀሳብ" የራዲዮ የመዝናኛ ፕሮግራም ስሜትን በመቀስቀስ አድማጭን እያበረታታ በማሳቅ መልዕክትን የማስተላለፍ ችሎታ አለው:: መዝናኛን ከይዘት አኳያ ስንመለከተው ከሌሎች ፕሮግራሞች ይልቅ የአድማጭን ስሜት እየቀሰቀሰ ለከፍተኛ ተሳትፎ የሚጋብዝ ነው::

### 3.1. በመዝናኛ ፕሮግራም የተነሱ አበይት ጉዳዮች

በ"ሀሳበ ለሀሳብ" በእሁድ የመዝናኛ ፕሮግራም የተላለፉት የለተያዩ ማህበረሰባዊ ጉዳዮች ህብረተሰቡን በማዝናናት መረጃና እውቀት የማስጨበጥ ባህሪ አላቸው:: እነዚህ የመዝናኛ ፕሮግራሞች የሚዳስሷቸው ጉዳዮች አሉ:: ስለሆነም የተላለፉትን በአምስት አብይት ጉዳዮች በመከፋፈል ከይዘት አኳያ ለመዳሰስ እሞክራለሁ::

#### 3.1.1. የፍቅር ግጥሞች

ፍቅር የሰው ልጆች ባህሪ ነው:: ፍቅር እንደአፍቃሪው ይለያያል:: በዕድሜ፣ በባህልና በአካባቢ ይለያያል:: አፍቃሪው እንደሚለየያይ ሁሉ የፍቅሩም አይነት ይተለያየ ነው:: የአገር ፍቅር፣ የእናት ፍቅር፣ የጓደኛ ፍቅር ወዘተ. አይነቱ ብዙ ነው:: በራዲዮ የመዝናኛ ፕሮግራምም የፍቅር ግጥሞች ላይ የተላለፉት በወጣትነት ዘመን ላይ የተመሰረቱ ናቸው:: በሚከተለው የፍቅር ግጥም እንመልከት::

የሚያፈቅሩትን ሰው መርሳት ይከብዳል
ያላየሁትን በአንች አይቻለሁ፣
የማላውቀውን አውቄአለሁ፣
ደካማ ጎኔን አጥንቻለሁ::
ስራም አልሰራ፣
ልቤ ከአንች ጋር እየተጣራ::
እንቅልፍም የለኝ፣
ሁሌም ከአንች ጋር ነኝ::
የተዋወኩበትን ቀን ስወቅስ እኖራለሁ፣
ደህና ሁኝ እያልኩሽ በእንባ እለይሻለሁ::

ዛሬም የቤት ስራ ነገም የቤት ስራ፣
አሳይመንት ስትሆኝ ሆነብኝ ኪሳራ::
በመጨረሻው ቀን ውሳኔ ፀደቀ፣
በአሉቧልታ ወሬ ፍቅራችን አለቀ::
አበበ ሞላ ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ
እሁድ ማታ 12:30 ህዳር 10/2001 ዓ.ም

የዚህ ግጥም ፅሀፊ የፍቅርን ሀያልነት ለሚወዳት ልጅ ብዙ ያላየሁትንና የማላውቀውን እንዲሁም ደካማ ጎኔን አስተምረሽኛል:: ነገር ግን በአንች ፍቅር ስለተጎዳሁ ስራ እንዳልሰራ፣ እንቅልፍ እንዳልተኛ፣ እረፍት ነስተሽኛልና የተዋወኩበተን ቀን ስወቀስ እኖራለሁ እያለ በመጨረሻም ፍቅሯ እንደቆረጠለት ይገልፃል::

የሚከተለውን “ውስብስብ” በሚል ርዕስ የቀረበውን የፍቅር ግጥም እንመልከት::

**ውስብስብ**

እንዳላናግርህ ፈረቸ፣
እንዳልተውህ ትግስት አጥቸ፣
ከራሴ ጋር እየተሟገትኩ፣
ድንገት ሳይህ በፈገግታህ ደነጥኩ::
የማልከፍልበትን ውበትክን እያየሁ፣
ራሴን በራሴ ስወቅስ እኖራለሁ::
ውበትክን ለማድነቅ ቢከፈለው ኖሮ፣
ምን ይበጀኝ ነበር ከእጄ ገንዘብ አጥሮ::
መሰረት ውቤ ከባህርዳር
እሁድ ማታ 12:45 ህዳር 5/2001 ዓ.ም

የዚህ ግጥም ፅሀፊ ሴት በመሆኗ የምታፈቅረውን ልጅ ለማናገር እንደፈራች እና ለመተውም ደግሞ ልቧ አልቆርጥ እንዳለ እና ከራሷ ጋር እንደምትጋጭ ያስገነዝባል:: በመቀጠልም ልጅቷ የጓደኛ ፍቅር አሸንፏት እያለ በተጨማሪም የፍራቻዋንና የድህነትን ስሜት አንድ ላይ በማምጣት ለምታፈቅረው ልጅ በብዕሯ ፍቅሯን ገልፃለታለች::

### 3.1.2. ቀልድ

ቀልድ አንድን ሰው የሚያስገርመውን ያህል ሌላውን ሰው ደግሞ ሊያስገርመው ይችላል:: በአንድ ወቅት በራዲዮ የመዝናኛ ፕሮግራም የተላለፈው ቀልድ በሌላ ጊዜ የማያስገርም ይሆናል:: በአንድ ቦታ አስገራሚ የሆነ ነገር በሌለኛው ቦታ ላያስገርም ይችላል:: ስለዚህ ቀልድ እንደየባህሉ የሚታይ ፈጠራዊና ህይወታዊ ገለፃ ነው:: የሚከተለውን እዚህ በታች እንመልከት::

*አንድ የታክሲ ተሳፋሪ ወደ-ማስጠጋት ቦታ ለመሄድ ሲል ታክሲዎች እየሞሉ ይመጣሉ:: ከዚያም "እነዚህ ታክሲዎች ደግሞ በሽታቸው ተነሳባቸው እንዴ?" በማለት ሀሳቡን ሲገልፅ ከጎኑ ያለው ተሳፋሪ "እንግዲህ በሽታው እንዳይጋባ መጠንቀቅ ነዋ?" አለ::*

*አብነት ሞላ ከጎንደር*

*እሁድ ማታ 12:30 ጥር 20/2001 ዓ.ም*

የዚህን ቀልድ ስናየው፤ በተናጋሪውና በመላሹ መካከል መግባባት እንዳልተፈጠረ ያሳያል:: ምላሽ የሰጠው ሰውየ የሰዎቸን ሀሳብ ያላገናዘበ በመሆኑ ተናጋሪውን አናዶታል:: ስለዚህ ይህ ቀልድ የሚያስተላልፈው መቀለድ የሌለበት ቦታ ላይ እንደተቀለደ ነው:: ምክንያቱም በሁለቱም ሰዎች መካከል አለመግባባትን ያሳያል:: ስለዚህ የሰዎችን ስሜት መጠበቅ እንዳለብን ያስገነዝበናል:: የሚከተለውን ደግሞ እንመልከት

*ሁለት ጓደኛሞች ምሳቸውን በዱባ ይበሉና ካበቁ በኋላ አንደኛው "እግዚአብሔር ይመስገን ብሎ ሲመርቅ:"* ሌላኛው ደግሞ "ለምን እግዚብሄርን *ታመሰግናለህ?* አለው "ሆዴ ስለሞላ ነዋ ብሎ ሀሳቡን ሲመልስለት ነገበቅል እስኪአበላህ ትጠብቃለህ" አለው::

*ታደሰ ቀለብ ከሀሙሲት*

*እሁድ ማታ 12:30 ጥቅምት 15/2001 ዓ.ም*

ይህ ለራዲዮ መዝናኛ በምልልስ መልክ የቀረበው ቀልድ እግዚአብሔርን ማመስገን ትልቅ በረከት እንደለው እና ያለ እግዚአብሄር የማይሆን ነገር የለም ሁሉም ይሳካል ይላል:: በሌላኛው ደግሞ አሁን እየኖርን አይደለም ንሮአችን የከፋ ነው:: ስለዚህ እግዚአብሔርን

ማመስገን የለብንም ይላል:: የዚህን ቀልድ ፅሁፊ ስሜት በትክክል ለማወቅ ቢያስቸግርም ከበስተጀርባው የንሮን አለመመቻቸት ማለትም፤ ድህነትን ይገልፃል::

### 3.1.3. የፍቅር አባባሎች

የሚከተለው የፍቅር አባባል ከዚህ በታች ቀርቧል::

ፍቅር ማሸነፍ ነው:: ቢሆንም ግን የበለጠ
መሰቃየት ነው::

ውብነሽ ውጩ ከአዲስ ዘመን
እሁድ ማታ 12:25 የካቲት 2/2001 ዓ.ም

ከዚህ በላይ በቀረበው ጥቅስ እንደምንረዳው የፍቅር አባባል አቅራቢ የፍቅርን ሀያልነት ይገልፃል:: ሴትም ትሁን ወንድ በፍቅር ከገባ/ች ይሸነፋል ወይም ትሸነፋለች የሚሉት ደግሞ በፍቅር ከገባች ወይም ከገባ የበለጠ መሰቃየት ነው:: ስለዚህ ብዙ ፈተናዎችን እንደሚያጋጥማቸው ያስገነዝባል:: የሚቀጥለውን የፍቅር አባባል ደግሞ እንመልከት::

በፍቅር የተሞላ ቃል በችግር
የወደቀውን የሰው ልጅ ህይወት
መለወጥ ይችላል::

መምህር ጌትነት ቢያድጎ ከእብናት
እሁድ ማታ 12:40፣ ጥር 11/2001 ዓ.ም

ፍቅር በሰዎች ላይ የሚያስከትለውን ለውጥ የጥቅሱ አቅራቢ ለማሳየት ሞክሯል:: በመፈቃቀር ብዙ ለውጥ ይገኛል:: ይህ ማለት ፍቅረኛውን አፍቅሮ የተሰቃየ ወጣት ከሄደት በኋላ ፍቅረኛው እሺ ብትለውና በፍቅሯ ሲሰቃይ የነበረው ህይወቱ እንደሚለወጥ ይገልፃል:: ስለዚህ በፍቅረኛሞች ችግር ቢፈጠር ተመልሰው ወደ ፍቅር እንደሚመለሱና በችግር የወደቀውን ስሜታቸውን እንደሚጠነክርና ለውጥ እንደሚያስገኝ ግንዛቤ ሰጥቶ ገልጿል::

ፍቅር በንፁህ ልቦናና በንፁህ
አዕምሮ የሚቀበሉት የአእምሮ ልብስ ነው::

መብራት ሙሀመድ ከባህርዳር

እሁድ ማታ 12:10 ታህሳስ 25/2001 ዓ.ም

የዚህ ጥቅስ አቅራቢ ፍቅርን ማንም ሊያስገድደው የማይቻል አንዴ በንፁህ ልብ የተወሰነ ፍቅር ዘላቂነት እንዳለው ይናገራል:: አዕምሮው አምኖበት ከልቡ ካፈቀረ ማንም ሰው ጓደኛውን ሊያስተወው ወይም ሊያስተዋት የማይቻል መሆኑን በዚህ የፍቅር አባባል ተገልጿል:: በመቀጠልም አፍቃሪው ሲያፈቅር አምኖበት የሚቀበለው የአእምሮ ስራ መሆኑን የአእምሮ ልብስ ነው በማለት ይገልፃል::

### 3.1.4. ደብዳቤ

ደብዳቤ የሰው ልጅ ሀሳቡን በፅሁፍ የሚገልፅበት አንዱ መንገድ ነው:: ደብዳቤ ተራርቀው ለሚኖሩ ሰዎች ለመገናኘት አመችነት የሌለው ከሆነና በስልክ ለማይመች እንዲሁም ብዙ ሀሳብ ለሚዝ መልዕክት ለሴት ፍቅረኛም ሆነ ለወንድ ጓደኛ ደብዳቤ በመፃፍ መልዕክቱን ማድረስ ይቻላል:: በተጨማሪም በራዲዮ የመዝናኛ ፕሮግራም ላይም አድማጮች መግለፅ የሚገልጉትን ለፍቅረኛቸው ደብዳቤ በመፃፍ የውስጥ ስሜታቸውን በመተንፈስ መልዕክቶቻቸውን በማስተካለፍ ይደሰታሉ::

ይህን የፍቅር ደብዳቤ በራዲዮ ፕሮግራም በሚያደርሱበት ጊዜ ፍቅረኛው ወይም ፍቅረኛውን ምን ያህል እንደሚወዳት ወይም አንደምትወደው ማረጋገጥ ይችላል:: ደብዳቤው በሚፃፍበት ጊዜ ውብና በተመረጡ ቃላት እንዲሁም በተመረጡ ሀሳቦች አሳምረው በመፃፍ መልዕክቱን በማድረስ ነው:: ከዚህ በታች የቀረበውን እንመልከት::

*ይህን ደብዳቤ ስፅፍልሽ እንባዬ ወረቀቱን እያራሰው ነው:: በሀሳቤ ስስስምሽ፣ ሳቅፍሽ እየታየኝ ነው:: ዋ! እንዴት አይነት ጥልቅ ስሜት ነው:: በሀሳቤ ሚሊዮን ጊዜ ስሜሻለሁ:: ደህና ሁኝ እንዳልልሽ ስንብቴ እስከ መጨረሻው ስለሚመስለኝ ትቼዋለሁ::...*

*አፍቃሪሽ አስራት ቸኮለ ከደንግላ ለአያልነሽ ገበሬ*

*እሁድ ማታ 12:25 ህዳር 13/2001 ዓ.ም*

የዚህ ደብዳቤ ፀሀፊ ወንድ ነው:: ዋና ቁምነሩም ለፍቅረኛው ታማኝ'እንደሆነ ከልቡ እንደሚወዳት ይገልፃል:: እንዴት እንደሚያፈቅራት መግለፅ በማይችለው ቃል በእንባ እያለቀሰ እንደሚፅፍላትና በሀሳብ ትዝ እንደምትለው፣ ደህና ሁኝ እንዳልልሽም ጨርሰሽ የምትለይኝ ስለሚመስለኝ ደህና ሁኝ አልልሽም በማለት ሀሳቡን በደብዳቤ ለሚወዳት ፍቅረኛው ያስተላልፋል:: ስለዚህ ዋናው ቁም ነገሩ መተሳሰብንና ታማኝነትን ያሳያል::

ለእኔው ውድ ፍቅሬ ለሄለን እንኳን ለገና በአል አደረሰሽ:: ቃላቶችን ለመፃፍ አንችን የማደንቅበት ቃል አጥቼ እንደባዮሎጂ የሸመደድኳቸው ሁሉ ጭራሽ ጥፋት አሉብኝ:: አንድ መስመር ለመፃፍ ስሰርዝ ስደልዝ ብዙ ደቂቃ ሆነብኝ:: አንችን ካፈቀርኩ ቀናቶችም ወራቶችም አልፈው ይኸው ዛሬ ድረስ አለሁ:: … አንች እኔን ላታስቢኝ ትችያለሽ እኔ ግን የህይወቴ ህይወት የመጀመሪያየም የመጨረሻዬም ሄሊን አድርግልኝ እያልኩ እግዚአብሔርን እየተማፀንኩ ለመንኩ::

አፍቃሪሽ ደ.አ ከደብረታቦር

እሁድ ማታ 12:45 ታህሳስ 29/2001 ዓ.ም

የዚህ ደብዳቤ ፀሀፊ ወንድ ነው:: የገናን በአል አስመልክቶ የተፃፈ ደብዳቤ ነው:: ሁሉም ሰው በአመትባል ወቅት ብዙ ነገር ትዝ እንደሚለው የዚህ ደብዳቤ ፅሀፊም ፍቅረኛው ትዝ እንዳለችው ፅፎላታል:: ሲፅፍላትም ልክ አንችን ሳስብ ለባዮሎጂ ትምህርት ያጠናኋቸው በሙሉ ጠፉብኝ ይላል::

ስለዚህ አንድ ሰው ለፍቅረኛው ደብደቤ ሲጽፍ የሚፅፈውን ነገር ፍቅረኛዮን ያስደስታታል ብሎ ማሰብ እንዳለበትና ሀሳብ ሲያወጣ ሲያወርድ እንዲሁም ሲሰርዝ ሲደልዝ በመጨረሻም ጥሩ ደብዳቤ ጽፎ ገልፆለታል:: እኔ ይኼን ያህል እወድሻለሁ አንች ግን እኔን ላታሰቢኝ ትችያለሽ እያለ ፍቅረኛውን ይጠራጠራል:: እኔ ግን የመጀመሪያዬም የመጨረሻዬም አንችን አድርጊልኝ እያለ እግዚአብሔርን እየተማፀነ ከልቡ እንደሚወዳት የገለፀ ነው::

### 3.1.5. ሙዚቃ

የአንድ ሀገር የስልጣኔ ደረጃ ሊገመትና ሊታወቅ የሚችለው የሀገሪቱ ዜጎች በፓለቲካ፣ በሀይማኖት፣ በኢኮኖሚ፣ በሞራል፣ በቴክኖሎጅና በመሳሰሉት አማካኝነት ሀገሪቱ ያላትን አድገት በመጠቀም ሲገልፁ ነው ማለት ይቻላል::

ሙዚቃም ከጭንቀት ለመዳን፣ ደስታን ለመግለፅ እና ስራን ያለመሰልቸት ተግተን እንድንሰራና እንድንዝናና ትልቅ አስተዋጽኦ አላት:: በተጨማሪም አንድን ሀገር ከሌላ ሀገር ባህሉን በመግለፅ የመገናኛ ዘዴ ጭምር ናት:: በአለም ላይ የሚኖሩ ሰዎች የሚገናኙበትና የሚዝናኑበት ልዩ ቋንቋ ናት:: በመጨረሻም የሰውን ልጅ የረቀቀ ውጤት ማስገኛ የምትሆን

የመንፈስ ምግብ ናት:: በ“ሀሳብ ለሀሳብ” የራዲዮ የመዝናኛ ፕሮግራምም የተላለፉት ሙዚቃዎች ብዙ ናቸው:: ከነዚህም ውስጥ ብዙዎቹ በፍቅረኞሞች የሚጋበዙ ናቸው:: ለአብነት ያህል “አለፈኝ” የሚለውን ሙዚቃ እንመልከት::

**እለፈኝ**

ቸኮልክ ልትግባባኝ
ሰንባችም አትመስለኝ ኗሪም አትመስለኝ
ብዙ ደርሶብኛል ብዙ ደርሶብኛል ተውአንታንገላታኝ
ልሙት መሞቱ አይከፋም ግዴለም ቅርብኝ
ምነው ብዙ ሳንቆይ ልሙትልሽ አልከኝ
አለኝ እለፈኝ እለፈኝ ላታዛልቀኝ
በኔም በሌላዋ የታዘብኩት አለኝ
ለአጭር ፍላጎትህ ተው አታመቻቸኝ
እለፍኝ እለፈኝ ብዙ አትደልለኝ
ጎዳናው ላይ ዋልኩኝ ተጓዡን ስቆጥረው
ይዞና አንጠልጥሎ ሂያጁን ስታዘበው
እኔ ብቻ ቀርሁ መንገዱን ልቃኘው
መውደድ ጥሎ ማለፍ ሆድ ሆዴን ሊያነደው
እህ ይለፈኝ ነው እህ ጠንቀቅ ነው::
ጊዜው ሰውም ፍቅር አቅል አሳጥቶታል
ነካ አርጎ መተውን ዝና አስመስሎታል
እለፈኝ እለፈኝ ጉዳይህ ገብቶኛል
ተዋዶ መውጣቱ መታየት ለአንድቀን
ለፍቅር ለጎጆ ምሰሶም ቋሚ አይሆን
እለፈኝ አለፈኝ መውደድ ለሰቀቀን
የኔና አንተም ነገር በልተከድኖ ይብሰል
ተዋደን ባንዘልቅ ተው አንበዳደል
ሳላይ ትካዜህን ሳይሆን ገንዘብ አንተዬ
ምነው ባይጀመር ለአጭር መተሳሰብ

ይቅርብኝ ተሰብሰብ

እህ አትምጣብኝ እህ ውስብስብ

ማርታ ሀይሉ::

ሰርካለም አባተ ከአዘዞ ለምስጋናው ሙጨ

እሁድ ማታ 12:35 ጥቅምት 9/2001 ዓ.ም

የዚህ ሙዚቀኛ ደራሲ ሴት ነች:: የይዘቱን መልዕክት ስናየው ፍቅረኛው ለማድረግ የፈለጋትን ልጅ ስለታሪኳ ምንም ሳያጠና በመቸኮል ሲጠይቃት እሷም በበኩሏ የቸኮለ አፍሶለቀመ ነውና ለኔ ልትሆን አትችልም:: ስለዚህ ለአጭር ጊዜ ነው የምታፈቅረኝ እናም ከልብህ አይደለም:: ከሌሎች ፍቅረኛሞች ብዙ ነገር ታምሬአለሁ ብትቀርብኝ ይሻላል በማለት በሙዚቃ ሀሳቧን ትገልፃለች:: ስለዚህ የሙዚቃው መልዕክት ችኩልነት እንደማይጠቅምና ልጅቷም ብዙ ግፍና በደል እንደደረሰባት ያሳያል:: የሚቀጥለውን "በማላውቀው" በሚል ርዕስ የቀረበው ሙዘቃ እንደሚከተለው ቀርቧል::

**በማላውቀው**

በማላውቀው በማላውቀው ነገር

ምነው ምን ቢሰማሽ

ኧረ እንዴት ቢከፋሽ

መች መጣሽ የትገባሽ

አንጀቴን በላሽ ስል አንጀቴ አላለቀም

ዛሬም ሳስቶልሻል በአንች ጤና አይደለም እረስቶሽ አልዋለም::

እረስቶሽ አላደረም

ልቤን በላሽው ስል ልብ አለኝ ልብ አልኩኝ

የት አለሽ ማን አየሽ ወዴት ልፈልግሽ ወዴት ላስፈልግሽ

ዛሬም ባክንኩልሽ

ተመችቶሻል ወይ ወይ ንሮ አስመረረሽ

አቀርቅረሻል ወይ እኔ አንገት ልድፋልሽ

አንችዬ ቸገረኝ ሳጣሽ ማን አየልኝ

አድሬ አንዳላገኘሽ ዝም ዝም ሆነብኝ

የት ልድረስ የት ላግኝሽ የትልጥራሽ

እህ ወይ አንጀቴ እህ እህ ወይ አንጀትሽ እህ እህ

እህ የት ልፈልግሽ

ጭር ባለው መንገድ መጣሁ ስንደረደር

ሀፍትም እንደከብት ሰው ይጋፋ ጀምር ዳር ይጥለኝ ጀመር

ይህን ለማንልንገር

እሷ ሆዴ ስትል እኔ አንጀቴ ስላት

ስትባክን ስባክን ወየሁ ገላማጣት ወየሁ ዘመድ ማጣት

ወዳጄን የትልጥራት

ደረጀ ደገፋው

አዳነ አለሙ ከደንበጫ ለፀሀዬ አዱኛ

እሁድ ማታ 12:40 የካቲት 25/2001 ዓ.ም

የዚህ ሙዚቀኛ ደራሲ ወንድ ነው:: የሙዚቃውን ይዘት ስንመለከት ከመጀመሪያው ፍቅረኛው ጋር እንደተለያየና በሩቅ ሀገር አንዳለች ይዘፍንላታል:: የትነው ያለሽው ተመችቶሻል ወይንስ ከፍቶሻል እያለ ምርር ትክዝ ብሎ እንደሚያፈቅራትና እንደሚዘፍንላት ይገልፃል:: ይህን ሙዚቃ በ"ሀሳብ ለሀሳብ" የመዝናኛ ፕሮግራም ላይ ለሚወዳት ፍቅረኛው የጋበዛት ምክንያት ከዚህ ሀሳብ ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ ነው:: በአጠቃላይ ከልቤ እወድሻለሁ የአለሽበትን ስፍራ ማን ይንገረኝ ጨነቀኝ ቸገረኝ የት ይሆን የማገኝሽ እያለ ከልቡ እንሚያፈቅራት በሙዚቃው ገልጾለታል::

## 3.2. በ"ሀሳብ ለሀሳብ" በራዲዮ በተለላፍ የመዝናኛ ፕሮግራም የቅርጽ ትንተና

የአንድን ግጥም ይዘት የምናስተውለው ገጣሚው ሊያስተላልፍ የፈለገውን ቁም ነገር በምን አይነት ቃላት ተጠቅሞ እንደሆነ በመገንዘብ ነው:: የቃለት አጠቃቀሙን እንዲሁም ግጥሙ ለዛ ባለው መልኩ እንዲደመጥለትና እንዲደነቅለት የሚያደርገው የግጥሙ ቅርፅ ጥሩ በሆነ መንገድ ሲቀርብ ነው:: ለዚህ ነው በግጥም ውስጥ ይዘትና ቅርፅ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ ናቸው የሚባለው:: ስለዚህ ይዘት ያለቅርፅ ሊታሰብ አይችልም:: ቅርፅም ያለ ይዘት ሊታሰብ አይችልም:: ልናስተላልፈው የፈለግነውን መልዕክት ጥሩ ቅርፅ ከሌለውና ጥሩ ቃላት ካልተጠቀምን ቁም ነገሩ ዋጋቢስ ይሆናል::

ለዚህም ነው ምርጥ ቃላትን አቀናብረን ጥሩ በሆነ መንገድ የአድማጮችን ስሜት በመረዳትና በመገንዘብ የምናቀርበው:: በዚህ መልክ ከቀረበ ተወዳጅነት ይኖረዋል:: በቀላሉም ሊረሳ አይችልም:: ስለዚህ ውበቱ ተጠብቆ እንዲተላለፍ ይጠቅማል::

በዚህ ጥናትም በ"ሀሳብ ለሀሳብ" የራዲዮ የመዝናኛ ፕሮግራም በተላለፍት የፍቅር ግጥሞች፣ ቀልጆች፣ የፍቅር፣ አባባሎች ደብዳቤዎችና ሙዚቃዎችን ከቅርፅ አንፃር ለመተንተን ስንነሳ ሁሉንም ነጥቦች ይደስሳሉ ማለት አይደለም:: በመግቢያው ላይ እንደተገለፀው የጥቂቶቹን በመውሰድ ለመተንተን ተሞክሯል::

### 3.2.1. የቃላት አጠቃቀም

ገጣሚዎች የራሳቸው የሆነ ቃላትን በመጠቀም ሊፅፉ ይችላሉ:: በራዲዮ የመዝናኛ ፕሮግራም አድማጮች መልዕክቶቻቸውን ለማስተላለፍ ሲሉ የትኛውን ቃል መጠቀም አለብኝ? በምን አይነት ብናቀናብረው ይቀላል? የሚሉትን ጥያቄዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት አለብን በማለት ይፅፋሉ:: በመሆኑም የመዝናኛውን ፕሮግራም ሳቢነት ከፍለማድረግ የመዝናኛው ፕሮግራም ተከታታዮች ቃላትን በተለየ አጠቃቀምና ቅንብር ሲገለገሉባቸው ይታያል::

የቃላት አጠቃቀም በምንገለገልበት ጊዜ አስፈላጊ ከሆኑት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው:: ድምፀቀድ ቃላት፣ ዘዮ ቃላት፣ ቃላተ ምሁር፣ ቃላተ ፈጠራ፣ ወለለት ቃላት፣ እንዲሁም ፋካሬያዊፍች ናቸው:: /ዘሪሁን አስፋው 1996:85/

ለጥናቱ በተመረጡት መፅሀፍት ውስጥ በራዲዮ መዝናኛ  ፕሮግራም የተላለፉትን ከቃላት አጠቃቀም አኳያ ስንመለከት በአብዛኛው ተለምዷዊ ቢሆኑም አንዳንዶቹ ደግሞ አዳዲስ ቃላት ተጠቅመዋል:: ከነዚህም ለጥናቱ የተመረጡት ቃላተ ፈጠራ፣ ዘዬ ቃላትና ዘይቤያዊ አነጋገር ናቸው::

#### 3.2.1.1. በፍቅር ግጥሞች

ገጣሚያን በግጥማቸው አመች በሆነ መንገድ አዲስና ያልተለመዱ ቃላትን ሲጠቀሙ ይታያሉ:: በራዲዮ የመዝናኛ ፕሮግራም ላይም የተላለፉት የፍቅር ግጥምች የሰመረ የቃላት አጠቃቀም አላቸው:: ከነዚህም በተጨማሪ ለአድማጮች ቃላቱን ከአጠቃላይ አውድ በማገናኘት ለመረዳት እንቅፋት የሚፈጥሩ ቃላት መሆን የለባቸውም::

"ቃል ገባሁ ለራሴ" በሚለው የፍቅር ግጥም የቀረበውን እንመልከት::

**ቃል ገባሁ ለራሴ**

ተውኝ ተውኝ ስለጓደኛ፣

ከእንግዲህስ ይሻላኛል ብቸኛ::

መዋቀሱ ምን ያደርጋል፣

የድሮው ፍቅር በጊዜው አልቋል፣

ደሞም ሆዴ ቆርጧል::

መቼ ነው ወደ ጓደኛ የምመለስ፣

ህልም መሰለኝ እውን ሲፈርስ::

አበራ ንጉሴ ከአዲስ ዘመን መሰናዶ ት/ቤት

እሁድ ማታ 12:35 የካቲት 21/2001 ዓ.ም

በዚህ የፍቅር ግጥም የገቡት ቃላት የተመረጡና የአድማጭን ጆሮ የሚስቡ ናቸው:: ገጣሚው የፈለገውንነገር ለመግለፅ በግጥሙ ውስጥ በተመረጡ ቃላት ሀሳቡን አንፀባርቋል:: በምርጥ ቃላትና ሀሳብ በይበልጥ በመጠቀም ለግጥሙ ውበት ሰጥቶ ሀሳቡን አጠናክሮ አሳይቷል:: የሚገልፀውም ሴት ፍቅረኛው እንደከዳችውና ከአሁን በኋላ ምንም አይነት ግንኙነት አያስፈልገንም ፍቅራችን በጊዜው አልቋል:: እያለ ገልፆታል:: ስለዚህ አንጄ የፈረሰ ነው እያለ በጥያቄ መልክ በምፅናቡ በመሳል ገልፆታል::

በመቀጠልም ምሳሌ ብንወስድና ብናየው የተሻለ ይሆናል:: "ሆዴ ቆርጧል":: የሚለውን ቃል ብንወስድ ከአሁን በኋላ ወደ አንች አልመለስም በማለት ከተለመደው አገላለፅ ጋር በማገናኘት በግጥሙ ውስጥ በመግለፅ ውበትና ጥንካሬን ሰጥቶት ይታያል::

ይህንኑ የፍቅር ግጥም ከዘዬ ቃላት ስናየው እንደሚከተለው ነው:: ዘዬ ቃላት አንድ ቋንቋ በሚነገርበት ቦታ መለያየት የተነሳ በሰዎች ቃላት አጠቃቀም ላይ የሚከሰት ልዩነት ነው:: ይህም ሲባል በአንድ ማህበረሰብ አካባቢ የሚነገር ዘዬ በሌላ ማህበረሰብ ከሚነገር ዘዬ የተለየ ነው:: ምክንያቱም በሚኖርበት ማህበረሰብ ወጉ፣ ልማዱ፣ ባህሉ ከአካባቢው ጋር የተገናኘ ስለሆነ ነው::

በመሆኑም ዘዬ ቃላትን በዚህ የፍቅር ግጥም ውስጥ ስናየው ለግጥሙ የበለጠ ውበት ከመስጠትና መልዕክቱንም ከማጉላት ባሻገር የግጥሙን ተናጋሪ ማንነት ወይም አካባያዊ ይጠቁማል:: ለዚህም ምሳሌነት የምንወስደው "ደሞም" የሚለውን ቃልስንመለከት የጎጃም ዘዬ መሆኑን ተንፀባርቆ እናየዋለን:: ቃሉም "ደሞም" የሚለው በተጨማሪም እንደማለት መሆኑን ያስገነዝባል::

እንዲሁም ከዘይቤ የቋንቋ አጠቃቀም ስናየው ደግሞ የሚከተለውን ይመስላል:: ዘይቤ በስነግጥም አይቀሬ የሆነ የቋንቋ አጠቃቀም ነው:: ዘይቤ መልዕክትን ለማጉላት ሲባል ከተለመደው የቋንቋ አወቃቀር ወጣ ባለ መልኩ ማቅረብ ነው:: ይህም ሲባል ከቋንቋ አወቃቀር ወጣ ባለ መልኩ ብቻ የሚቀርብ ነው ለማለት አይደለም:: ከላይ በቀረበው በራዲዮ የመዝናኛ ፕሮግራም ዘይቤውን ሰናይ እንደሚከተለው ቀርቧል::

"ቃል ገባሁ ለራሴ" በሚለው የፍቅር ግጥም ገጣሚው በግጥሙ የምናውቀውን ነገር በሚስብ መልክና ውበት በአለው መንገድ ለማቅረብ ሞክሯል:: ጓደኝነት ጥሩ ፍቅር እንዳለው ሁሉ በተቃራኒው ደግሞ ጥላቻ እንዳለውና እንደተጣሉ ያስረዳል:: ለዚህም ጥቂቶች ሀረጎችን ብናይ "ተውኝ /2/ ስለጓደኛ ከእንግዲህስ ይሻለኛል ብቸኛ መወቃቀሉ ምን ያደርጋል የጊዜው ፍቅር በድሮው አልቋል::" የሚሉትን ስናይ ሰውኛ ዘይቤን ተጠቅሞ የሰውልጆች በህይወት የሚያጋጥሟቸውን ነገር መጣላት ሁለቱንም በሰውልጆች ያሉ ፀባዮች መሆናቸውን ሐሳቡን ተጠቅሞ ለመግለፅ ሞክሯል::

ሁለተኛው የፍቅር ግጥም "አዘኝልኝ የኔውብ" በሚል ርዕሰ የቀረበውን እንመለከት::

**እዘኝልኝ የኔውብ**

ልቤ ተጨናንቆ አይኔ ስንከራተት፣
ሳቂበት ጥርሰሽን እፎይ ልበልበት::
        ሀሳቤን አስቤ ጉዞየን ካንቺ ጋር
        ምንኛ ተከፋሁ ሳላገኝሽ ስቀር::
እዘኝልኝ እንጅ የውስጤን ተረድተሽ፣
እንግዲህ ያለ እኔ አንችስ ምን ሰው አለሽ::
አልረታም ብዬ በልቤ ስኩራራ፣
በኔ ደረሰብኝ ልሄድ ነው ልጣራ::
ልቤ ይመኝሻል አይኔም ፈልጎሻል፣
የእኔ እንደምትሆኝ በእርግጥ ተረድተሻል፣
ተረጅልኝ እንጅ ጣልጣል አታርጊኝ፣
ከአንድ አምላክ ተፈጥረን እንዴት ሰው አላግኝ::
        አምላኩ ጫኔ ከጎንደር ለሰናይት
        እሁድ ማታ 12:45 ህዳር 5/2001 ዓ.ም

በዚህ የፍቅር ግጥም ገጣሚው በሀሳቡ ያሰበውን ነገር ውበት በአላቸው ቃላቶች በመጠቀም በቀላሉ እንዲነበብ አድርጎ በግጥሙ አንፀባርቆታል:: በዚህም መሰረት አንድ አፍቃሪ የሚያፈቅራትን ልጅ ውበት ሲገልፅ አፍቃሪው እየፈለጋትና በድንገት ሲያያት በጥርሷ ፈገግታ እንደሚደሰት ወደ እሷ ለመሄድም ሲያስብና ከሄደም በኋላ እንደማያገኛትና እንደሚከፋው ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት ውበት ባለው የቃላት ፈጠራ ተጠቅሞ ለመግለፅ ችሏል::

በተጨማሪም ፍቅረኛውን እንደሚያፈቅርና እንደሚፈልጋት በማድረግ አይኔ “ሲንከራተት” በማለት በተመረጠ ቃል በመጠቀም የፍቅር ግጥሙን ለዛ እንዲኖረውና አንባቢንና አድማጭን ትኩረት ሰጥቶ እንዲደመጥ አድርጎ ገልፆታል::

በመቀጠልም የዚህ የፍቅር ግጥም ዘይቤውን ስናይ በአማራ ክልል የሚነገር ዘዬ ነው:: ለምሳሌ ያህልም “እዘኝልኝ የኔ ውብ” በሚል ርዕስ ካቀረበው ቃል “አልረታም” የሚለውን ነው:: ቃሉም አልሸነፍም በማለት ፈንታ አልረታም የሚለውን ቃል ተጠቅሞ ለመግለፅ ሞክሯል::

የዘይቤ አጠቃቀሙን ስንመለከት ሰውኛ ዘይቤ ተጠቅሞ ለመግለፅ ሞክሯል:: የተወሰኑትን ሀረጋትና ቃላት ብናይ፤ “አይኔ ሲንከራተት፣ እፎይልበልበት፣ እዘኝልኝ” የሚሉትን ሰናይ የሰውልጆች የሚያከናውኗቸውን ፀባይ በተመለከተ በመግለፅ ሰውኛ ዘይቤን ተጠቅሞ ለመግለፅ ሞክሯል::

### 3.2.1.2. ቀልዶች

ቀልዶችን በራዲዮ የመዝናኛ ፕሮግራም ሲቀርቡ በተመረጡ ቃላትና ውብ በሆኑ ሀሳቦች ተቀናብረው ለአድማጮች ጆሮ በሚስብ መልክ ሲቀርቡ ያሳዝናሉ አለያም በጣም ያስቃሉ:: ከነዚህም ሁለት ያህል ቀልዶችን ከዚህ በታች እንመልከት::

ጫት ቃሚዎችን ፍየሎቹ ክፉኛ አስጠነቀቁ::

መምህር እሸቱ አየለ ከደንበጫ

እሁድ ማታ 12:50 ጥቅምት 10/2001 ዓ.ም

የዚህ ቀልድ ፅሀፊ “ፍየሎች” ሰዎችን ጫት መቃም እንደሌለባቸው ይገልፃል:: ስለዚህ ቅጠልን መብላት ያለባቸው ፍየሎች ናቸው ይላል:: ፍይሎች ለሰዎች ማስጠንቀቂያ እንደሰጡ ይገልፃል:: በተጨማሪም ይህን ቀልድ ፀሀፊው ሲያቀርብ በተመረጡ ቃላትና ፍየሎች ሰዎችን

በጣም እንዳማረሩ ሲገልፅ “ክፍኛ አስጠነቀቁ” በማለት በአዲስ ቃል ያሰበውን በሚስብና በሚያዝናና መልክ ለመግለፅ ሞክሯል::

ከዘዬ ቃላት ስንመለከት ደግሞ ከዚህ ዘዬ ነው ብሎ ለመመደብ ያስቸግራል:: ምክንያቱም በአንድ አረፍተ ነገር ስለቀረበ ግልፅ የሆነ ዘዬ የለውም::

እንዲሁም ከዘይቤ አንጻር ስንመድበው፤ ከአነፃፃሪ ዘይቤ ተመድቦ ይገኛል:: የቀልዱ ጽሀፊ ፍየሎችንና ሰዎችን በማነፃፀር ለመግለፅ ችሏል:: በተጨማሪም ፍየሎች ብቻ ናቸው ቅጠል መብላት ያለባቸው:: ሰዎች ግን እንደፍየሎች ጫትን መጠቀም የለባቸውም በማለት ሁለቱን በማወዳደርና በማነፃፀር ለመግለፅ ችሏል::

ሁለተኛውን ቀልድ ደግሞ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ይቀርባል::

እባክሽ በጉ እየጮኸ ነው ሳይለንት አድርጊልኝ?

ትግስት አበበ ከጐንደር

እሁደ ማታ 12:45 ታህሳስ 59/2001 ዓ.ም

የዚህ ቀልድ ፅሁፊ ሊገልፅ ያሰበውን ሀሳብ በተመረጠ ቃል እንዲሁም በተመረጠ ሀሳብ ለአድማጮች ይበልጥ እንዲዝናኑ በማድረግ ገልፆታል:: ይህም “በጉ እየጮኸ ነው ሳይለት አድርጊው” ሲል ቀልድ እንደሆነ ይታወቃል:: “ሳይለት” ለምባይል እንደሆነ እናውቃለን ስለዚህ አድማጮች የበለጠ ይዝናናሉ ብሎ ለመግለፅ ያሰበውን በቀልድ ውስጥ ገልፆታል::

ከዘዬ ቃላት ስንመለከት ከዚህ ዘዬ ይመደባል ለማለት ግልፅ አይደለም:: ምክንያቱም የቀረበው ቀልድ በአንድ አረፍተ ነገር ስለቀረበ ከላይኛው ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ ዘዬ የለውም::

ዘይቤውንም ስናየው ከአንደኛው ቀልድ ጋር ተመሳሳይ ነው:: የበጉን ድምፅ ከሞባይል ጋር በማወዳደር ከአነፃፃሪ ዘይቤ በመመደብ ለመግለፅ ችሏል:: በተጫማሪም በአመትበአል ወቅት የተገዛን በግ እየጮኸ ሲያስቸግር በቀልድ መልክ “ሳይለንት” አድርጊው በማለት ከሞባይል ጋር አነፃፅሮ የተገለፀ ነው::

### 3.2.1.3. የፍቅር አባባሎች

ስለፍቅር ብዙ ተብሏል:: በራዲዮ የመዝናኛ ፕሮግራም የቀረቡትን የፍቅር አባባሎችን ከቅርፅ አንፃር ስንመለከት ውብ በሆኑ ቃላት የሚፃፍና የሚያስተላልፉት መልዕክትም ቅርፁን የጠበቀ ካልሆነ በጥሩ ሁኔታ የሚደመጡ አይሆኑም:: የሚከተሉትን ከዚህ በታች እንመልከት:: “እንትናየ” በሚል ርዕስ የቀረበውን እንመልከት::

**እንትናዬ**

*እውነተኛ ፍቅር ቢተውት የማይተው የማይሰለችና*

*ውስጥ ውስጡን የሚቦረቡር እሳት ነው::*

*ቸርነት እንግደው ከጣና ሀይቅ ት/ቤት*

*እሁድ ማታ 12:35 የካቲት 3/2001 ዓ.ም*

*ዕሀፊው ስለቅር ሲፅፉ ለጆሮ አድምጡኝ አድምጡኝ በሚያሰኙና ለዛ በአላቸው ቃላት ተጠቅሞ አቅርቧል:: እውነተኛ ፍቅር ሁሌም የማይሰለችና ውስጥ ውስጡን እንደ እሳት የሚያቃጥል ነው በማለት አንባቢን ትኩረት ሰጥቶ እንዲያዳምጠው አድርጎ ገልጿል:: የምናውቀውን ነገር በበለጠ ለዛና ውብ በሆኑ ቃላት ለመግለፅ ችሏል::*

*ከዚህ የፍቅር አባባል ከዘዬ ቃላት አጠቃቀም ስንመለከተው ከዚህ የአነጋገር ዘዬ ይመደባል ብሎ ለመናገር ያስቸግራል:: የሚታወቅ ዘዬ የለውም::*

*ከዘይቤአዊ አነጋገር ሲታይ ደግሞ ተለዋጭ ዘይቤ አካቶ ይታያል:: ይህ የሆነበትም ፍቅር በሰዎች አማካኝነት የሚደረግ የተግባቦት ሂደት ነው:: ነገር ግን የዚህ የፍቅር አባባል ፀሀፊ በሰዎች የሚካሄደውን የተግባቦት ሂደት "ለእሳት" በመስጠት ከተለዋጭ ዘይቤ ተመድቦ ይታያል::*

*ሁለተኛውን ደግሞ "ፍቅሬ ሆይ" በሚል ርዕስ የቀረበውን እንመለከት*

**ፍቅሬ ሆይ**

*እውነተኛ ፍቅር በሰዎች አስገዳጅነት ወይም በአንድ ሰው*

*የግል ጥቅም ወይም ሰሜት ሳይሆን ከአምላክ የሚሰጥ ፀጋ ነው::*

*ታምራት ከእብናት*

*እሁድ ማታ 12:20 ጥር 15/2001 ዓ.ም*

*ከዚህ አባባል እንደምንረዳው ጽሀፊው እውነተኛ ፍቅርን ከሁልጊዜው በተለየ መንገድ ለመግለኝ ሞክሯል:: "እውነተኛ ፍቅር በአንድ ሰው አሰገዳጅነት በግል ጥቅምና በስሜት ሳይሆን ከአምላክ የሚሰጥ ትልቅ ፀጋ ነው::" በማለት ሀሳቡን ገልጿል:: በመሆኑም እውነተኛ ፍቅር አስበውበት ሳይሆን ከእግዚአብሄር የሚሰጥ ፀጋ መሆኑን አዳዲስ ቃላትን ተጠቅሞ ለአንባቢ በሚስብ መልክ አቅርቧል::*

ዘዬውንም ስንመለከት ከላይኛው የፍቅር አባባል ተመሳሳይ ነው:: ስለሆነም ከዚህ የአነጋገር ዘዬ ይመደባል ብሎ ለመናገር ያስቸግራል:: ስለዚህ የሚታወቅ ዘዬ የለውም::

እንዲሁም ዘይቤአዊ አነጋገሩም ሰውኛ ዘይቤን ተከትሎ የተገለፀ ነው:: "እውነተኛ ፍቅር በሰዎች አስገዳጅነት ወይም በሰዎች የግል ጥቅም እንዲሁም በስሜት ሳይሆን በእግዚአብሔር የሚገኝ ፀጋ ነው" በማለት ይገልፃል:: ስለዚህ የሰው ልጆችን ባህሪ ተከትሎ የተገለፀ ስለሆነ ሰውኛ ዘይቤ ልንለው እንችላለን::

### 3.2.1.4. ደብዳቤዎች

ስለደብዳቤ ምንነት በ3.1.4 በይዘቱ ክፍል በተገለፀበት በሰፊው ተብራርቷል:: በራዲዮ የመዝናኛ ፕሮግራም የሚቀርቡት ደብዳቤዎች ከቅርፅ አኳያ ስንመለከት አድምጡኝ አድምጡኝ የሚያሰኙና የአድማጮችን ተሳትፎ የሚያበረታቱ ናቸው:: ከነዚህም የፍቅር ደብዳቤዎች በፕሮግራሙ ይተላለፋሉ:: እነዚህን ደብዳቤዎች ቅርፃቸውን ስንመለከት ከዚህ በታች ቀርበዋል::

> ለእኔ ፍቅር ትላንት የአንቺን ፍቅር የተጠማሁትን ያህል ዛሬ ላይሆኜ ሳስብ ለእኔ ያለሽን ፍቅርና ታማኝነት እንዲሁም ቃል ጠባቂነትሽና ግልፅነትሽ ለኔ ትልቅ ደስታን እንድፈጥር አድርጎኛል:: ለእኔ ያለሽን ፍቅር ከመጠበቅሽ በአሻገር እኔም ለአንቺ ያለኝ ፍቅር እስከ ወዲያኛው አለም ሁሌም ለዘላለም እንደማፍቅርሽ እወቂልኝ ብያለሁ:: የኔ ፍቅር በአንድ ወቅት በዚያ በሚጣፋጠው አንደበትሽ ያለሽን ፍቅር "እወድሀለሁ አይዞህ የኔ ፍቅር ለዘላለሙ ከአንተ የሚለኝ የለም:: ሁሌም በውስጤ ትኖራለህ ሁለመናዬ የግልህ የብቻህ ነው::" አልነበርያልሽኝ:: አዎ ለአንቺ ያለኝን ፍቅር ለመግለፅ አቅሙ ባይኖረኝም በተግባር ለመተግበር ግን "አልዋሽም እኔ አልዋሽም የእምነት ቃሌን ክጄ አላበላሽም" የሚለውን የንዋይን ዜማ በእኔ ስም አድማጭልኝ እያልኩ የመዝጊያ ደብዳቤዬን ቀጥዬ ልገልፅልሽ እወዳለሁ:: የኔ ቆንጆ ብዙ እንዳልፅፍልሽ የብረት አለሎ የመሰለውን አይንሽን ማድከምና የጥናት ጊዜሽን መሻማት ስለሚሆንብሽ ቻው::
>
> ፍቅረኛሽ ደረጀ መኮንን ከጎንደር ለሙልየ
>
> እሁድ ማታ 12:40 ታህሳስ 25/2001 ዓ.ም

የዚህ ደብዳቤ ፅሀፊ ለሚወዳት ፍቅረኛው በሚስብ መልክ ሀሳቡን ገልጿል:: የቃላት አጠቃቀሙን ስናይ፤ "ፍቅርሽን የተጣማሁ፣ አይዞህ የኔ ፍቅር የአንተ ብቻ ነኝ::" እንዲሁም በመጨረሻው የገለፀው ሀሳብ "የብረት አለሎ" የመሰለውን አይንሽን በሚሉት ውብ ቃላቶች ተጠቅሞ ለፍቅረኛው ለዛ በአለው አገላለፅ ደብዳቤውን አቅርቧል::

ዘዬውም ከዚህ የአነጋገር ዘዬ ይመደባል ለማለት ያስቸግራል:: ምክንያቱም ከዚህ ዘዬ ይመደባል ብሎ መናገር አያስችልም:: ስለዚህ ዘዮዎቹ በጉልህ አይታወቁም::

ከዘይቤአዊ አነጋገር ስናየው አነፃፃሪ ዘይቤን አካቶ ይገኛል:: ምክንያቱም "የብረት አለሎ የመሰለውን አይንሽን ማድከም ስለሆነብኝ" የሚለውን ሀሳብ ሰንመለከት የልጅቱን /የፍቅረኛውን/ አይን ትልቅነት "ከአለሎ" ጋር በማነፃፀር በደብዳቤው ተገልፆ ይታያል:: የቀጥለው ደግሞ ከዚህ በታች ቀርቧል::

> እንዲህ ነበር እቅዳችን የኔ ውብ አይኖችን ጨፍኜ ትላንት ያልሻቸውን ሀሳብ ሳስብ ከልቤ አልጋ ላይ አንችን የረሳሁበት አንድም ቀን የለኝም:: ዘወትር ከህሊናዬ ለማትጠፊው ውድና ተናፋቂ ፍቅረኛዬ ለማህሌት እንደምን አለሽ ከተለያየንበት ቀንና ሰአት ጀምሮ ለጤናሽ እንደምን ከርመሻል:: ማህሌት እኔ ደህና ነኝ ማለቱ ይከብደኛል:: ለምን ብትይ ናፍቆቱን አልቻልኩምና የወደፊት ህይወቴን ካንች ውጭ ማሰብም ሆነ ማለም አልችልም:: በጣም የሚያስፈራኝ ነገር ቢኖር አንቺ ህይወትሽን ከእኔ ውጭ ታስቢ ከሆነ ብዬ ማሰቤ ነው:: ግንኙነታችን ታድሶ ፍቅራችን እስከ መጨረሻው እንዲሆን ተስፋ አደርጋለሁ:: ማህሌትዬ ምን በደልኩሽና ነው ይህን ያህል ድምፅሽ የራቀብኝ ማህሌት እኔም እንዳአንቺ ደምያለኝ ሰው ነኝ:: እባክሽ ጭካኔሽ ይብቃ:: ያጠፍሁት ካለ ልካስ:: አልያም በህግ ልቀጣ:: ውድፍቅሬ እስከመቸም ቢሆን ፍቅርሽ በልቤ ይኖልና መላበይኝ::
>
> አፍቃሪሽ አምሳሉ ሀይሉ ከሀሙሲት
>
> እሁድ ማታ 12:40 ታህሳስ 25/2001 ዓ.ም

ይህ ደብዳቤ ለሚወዳት ፍቅረኛው የተፃፈ ነው:: ሆኖም ፍቅረኛውን ለማሳመን በሚያደርገው የቃላት ምርጫ ስናየው፤ "እንዲህ ነበር እቅዳችን" በማለት በመግቢያው ላይ የወደፊት ኑሮውን ከፍቅረኛው ጋር ምን እንደሚመስል እና ተገናኝተው በነበረበት ጊዜ

ፍቅረኛው ያወራችውን በምዕናቡ እያስታወሰ በደብዳቤው ገልፆታል:: በጨማሪም "እኔም እንደ አንች ደም ያለኝ ሰው ነኝ" የሚለውን ሀሳብ ስንመለከት፤ እኔም እንደአነቺ ቀይ ነኝ ለምን እሺ አትይኝም:: አታንገላችኝ እያለ በምዕናቡ ቃላቶችን በመሳል በተመረጡ ሀሳቦችና ቃላቶች በመጠቀም ለመግለፅ ሞክሯል::

ዘዬውን ስንመለከት ደግሞ ከአንደኛው ዘዬ ጋር ተመሳሳይ ነው:: ዘዬው በጉልህ አይታወቅም ስለዚህ ዘዬ የለውም::

እንዲሁም ከዘይቤ የአነጋገር አይነቶችም ስናየው፤ ተለዋጭ ዘይቤን አካቶ ይገኛል:: ለምስክርነት ያህል ብንወሰድ፤ "ከልቤ አልጋ ላይ" የሚለውን ቃል ስናይ፤ ሁሌም ፍቅርሽ በልቤ ይኖራል:: እያለ በልቤ አልጋ ላይ በማለት የሰውን ልጅ ልብ እንደ አልጋ በመውሰድ በተለዋጭ ዘይቤ በመጠቀም ሳቢነት ባለው ሀሳቡን አጠንክሮ ገልጿል::

#### 3.2.1.5. ሙዚቃ

ስለሙዚቃ የይዘቱ ትንታኔ በተሰጠበት ክፍል ተገልጿል:: በ"ሀሳብ ለሀሳብ" የመዝናኛ ፕሮገራም በሚቀርብበት ጊዜ አድማጮች እንዳይሰለቹ ሙዚቃ ማስተላለፍ አስፈላጊነው:: በዚሁ ፕሮግራም የቀረቡትን ሙዚቃዎች ከቅርፅ አንፃር የቃላት አመራረጣቸውና የሀሳብ ፍሰታቸውን ስንመለከት እንደሚከተለው ከዚህ በታች ቀርበዋል::

**ምናለ ከደላሽ**

እቴ አስችሎሽ ለመድሽ ወይ ከሌላ
        አብሮም እንዳልበላ
        ለመድሽ ወይ ተመቸሽ
        ከረምሽ ወይ ተስማምቶሽ
እህ አንችም እንደሌላ
        ለመድሽ ወይ ከሌላ
ተለየሽኝ ብየ እንደአላማሽ ለሰው
ለሰሚም ገልጬ እንዳልተፋሰው
ይስጥሽም እንዳልል የኔን እንጉርጉሮ
ሰው መንገደኛ ነው ይገናኛል ዞሮ
        እሆዴ ላይ ዘፍ አትበይ ተነሽ ካንጀቴ
        ከሰው ገላ ያልምድሽ እኔም አከላቴ

ጥሩ ኩታም አግኝተሽ ለብሰሽ ከሞቀሽ

በይ ይሁና ምን አለ ለአንቺ ከደላሽ

ከተሰማማሽ ከደላሽ ምናለ ከደላሽ

ከሞላልሽ ከቀናሽ ምናለ ከቀናሽ

ለአንቺ ከሆነልሽ ከተመቸሽ ኑሮ

እኔም ሰውነኝና ሰው ልልመድ ዘንድሮ

ፍቅር ያላገሩ የትም አያደርስም

ደሞ ቀና ብዬ ቤቴን አላፈርስም

ከኔምሌላ ካገኘሽ በፍቅር በፀባይ

እዘዥበት ያን ገላ ወጥተሽ ከአደባባይ

ያልብሽን አግኝተሽ ከተደላደልሽ

ከተስማማሽ ምን ከፍቶኝ አንችን ከደላሽ

አዝማች----------------

አረጋኸኝ ወራሽ

በሪሁን ከዳንግላ ለደመቁ

እሁድ ማታ 12:35 ጥቅምት 9/2001 ዓ.ም

የዚህ ሙዚቃ ደራሲ የተጠቀመባቸው ቃላቶችና ሀሳቦች የተመረጡ ናቸው:: ከእነዚህም የተወሰኑትን ብናይ፣ "እንጉርጉሮ፣ ከሆዴ ዘፍአትበይ፣ ከደላሽ፣ ከተስማማሽ፣ ከምላልሽ" የሚሉት ይገኙበታል:: እነዚህ ቃላቶችና ሀረጋት የሚገልፁት ከእኔ እርቀሽ አንችን ከተመቸሽ ይሁን አንችን አይክፋሽ እያለ በውብ ቃላቶቸ ሀሳቡን ተጠቅሞ በሙዚቃ ለመግለፅ ሞክሯል::

ከዘዬ የአነጋገር አይነቶች ስናየው ብዙም ጎልቶ የሚነገርበት ቦታ ባይጠቁም በአማራ ክልል የሚነገር ዘዬን ያካተተ ሙዚቃ ነው:: ለምስክርነትም "ደሞ" የሚለው ቃል በደቡብ ጎንደርና አልፎ አልፎ በጎጃም አካባቢ ይጠቀሙበታል::

ይህ ሙዚቃ ከሰወኛ ዘይቤ የአነገጋገር ስልት የተገለፀ ነው:: ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው የሰው ልጆችን ባህሪ የሚገልፅ ስለሆነ ነው:: ለምሳሌ:- ጥሩ ኩታም አግኝተሽ ለብሰሽ ከሞቀሽ" የሚለውን ሀረግ ስናይ፤ "ኩታን" ልክ እንደ ጥሩ ጓደኛ ካገኘሽ ይቅናሽ እያለ የሰውኛን ዘይቤ ተጠቅሞ የተገለፀ ነው:: ሁለተኛው ሙዚቃ ደግሞ ከዚህ በታች ቀርቧል::

**ትርፍ መዘዝ አለው**

የምንለቀቅ ለቀቅ የምንዘና ዘና

መጠንቀቅ ነው ደጉ ለአንተም ለኔም ጤና /3/

እንደልጅነትህ እንደልጅነቴ

ሳልነግርህ ለፍቅርህ በቀን ሶስት አራቴ

ግን ያገኘሽኝለት ቃሉን እንዳትረሳው

አንድ ሰው ላንድ ይሁን ትርፉ መዘዝ አለው

መዘዝ አለው /4/

እቃ እቃ እንጫወት ጎጆ ደጅ እንጥና

አባለሌ እንበል እጀን ያዘኝና

አንድ ለአንድ እንሁን አልይአትይ ሌላ

የዘመኑ ነገር መኘታው መች ደላ

አልይ አትይ ሌላ

መኘታው መች ደላ

አልይ አትይ ሌላ

የምንለቀቅ ለቀቅ አረገኝ ጠበቅ ጠበቅ

ነፍስ እንዳይገባ ላፍታ ስንላቀቅ

ከለመዱት ጦረን ከወደዱት ጋራ

እምነት ፍቅር ካለ ይገፋል ተራራ

ፍቅር ካለ ይገፋል ተራራ

እምነት ካለ ይገፋል ተራራ /2/

አስቴር አወቀ

በሶና አማረ ከባህርዳር ለM.A

እሁድ ማታ 12:40 የካቲት 25/2001 ዓ.ም

በዚህ ሙዚቃ ደራሲው የተጠቀመባቸው ሀሳቦችና ቃላቶች በአእምሮው ምዕናብ ፈጥሮ የልጆች ጊዜውን በማስታወስ ፍቅረኛዋን አንደምትወደው አድርጎ በሙዚቃ አቅርቧል:: የቃላት ፈጠራውን ስናየው ከርዕሱ በመነሳት "ትርፍ መዘዝ አለው፣ አባለሌ /አጮለሌ መኘታው መች ደላ፣ ነፍስ እንዳይገባ፣ ፍቅር ካለ ይገፋል ተራራ::" የሚሉት ቃላቶች ለሙዚቃው ውበት ሰጥተውት በጥሩ ሁኔታ እንዲቀናበር አድርገውታል:: የሁለቱን ፍቅረኞች እምነት ፍቅራቸውን በተመለከተ በሙዚቃ መልክ በሚስብ ሁነታ ለማቅረብ ሞክሯል::

ይህ ሙዚቃ የአማራ ክልል የአነጋገር ዘዬን ያካተተ ነው:: ለማስረገጫ ያህልም ብናይ፤ “አ፺ለሌ ወይም አጮለሌ” የሚለው በጎጃም ሞጣ አካባቢ ልጆች እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚጫወቱት የጨዋታ አይነት ነው::

ዘይቤውንም ስንመለከት ሰውኛ ዘይቤን ያካተተ ነው:: ምክንያቱም የሰው ልጆችን ባህሪ አጠቃሎ የያዘ ሀሳብ በመሆኑ ከሰውኛ ዘይቤ ሊመደብ ችሏል:: ከነዚህም መካከል፤ “አ፺ለሌ /አጮለሌ/” የሚለው ቃል የልጆችን ጨዋታ የሚገልፅ በመሆኑ ነው:: እንዲሁም “ነፍስ እንዳይገባ” የሚለውን ሀረግ ስናይ፤ በሁለቱም ፍቅረኞች መካከል ሌላ ሰው እንዳይገባ ለማለት “ነፍስ” የሚለውን ቃል ከሰው ልጅ ጋር በማነፃፀር በሰውኛ ዘይቤ ተጠቅሞ አቅርቦታል::

## ምዕራፍ አራት

### ሀ. ማጠቃለያ

በባህርዳር ከተማ በአማራ ብሄራዊ ክልል ድምፅ በሀሳብ ለሀሳብ የመዝናኛ ፕሮግራም በሚል ርዕስ አጥኚው ጥናቱ አቅርቧል:: በመጀመሪያ ሲነሳ ባስቀመጠው አላማ መሰረት በራዲዮ ጣቢዮው የተላለፉትን የፍቅር ቀልዶች የአድማጮችን ደብዳቤ የፍቅር አባባሎችንና ሙዚቃዎችን በመሰብሰብ ቅርፃቸውንና ይዘታቸውን በመመርመር ለመተንተን ነው ተብሎ ተገልጿል:: እንዲሁም ለራዲዮ ለመዝናኛነት ፕሮግራም መቅረብ አለባቸው ብለው የሚፅፉትን የፕሮግራም ተሳታፊዎችን ችሎታ የሚመረምር መሆኑንም ተገልጿል::

በመቀጠልም የንድፈ ሀሳብ ቅኝት በተመለከተ የመዝናኛ ምንነት ተገልጿል:: እንዲሁም በዚህ ክፍል የተዛማጅ ፁሁፎች ቅኝትን በተመለከተ አራት ዲማፆች ከዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር ዝምድና ያላቸውን በማወዳደርና በማነጻጸር አንድነታቸውንና ልዩነታቸውን በሰፊው ተዳሰዋል::

እነዚህን የመዝናኛ ፕሮግራሞች ይዘታቸውን ስንመለከት በአብዛኛው የወጣትነት ፍቅር የሚዳስሱ መሆናቸውን አይተናል:: በመሆኑም በፍቅር ግጥሞች፣ ደብዳቤዎችና ሙዚቃዎች የተነሱት ጉዳዮች የወጣቶችን ፍቅር የሚዳሰሱ ናቸው:: በመሆኑም በነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች የተነሱትን ስናይ አዝናኝነታቸው ጎልቶ የታየበት ነው:: በተጨማሪም የፍቅር አባባሎችንና ቀልዶችን ስናይ፤ አዝናኝነታቸው እና ይዘታቸው የጎላ አይደለም ስለዚህ ዝቅ ያለ ግምት የሚሰጣቸው ናቸው::

በመቀጠልም ከቅርፅ አንፃር ደግሞ፤ የቋንቋ አጠቃቀማቸውን ስንመለከት በፍቅር ግጥሞች፣ ደብዳቤዎችና ሙዚቃዎች የበለጠ የቃላት የሀሳብ እና የዘዬ እንዲሁም የዘይቤያዊ አገላለፃቸው ከፍተኛ ነው:: በመሆኑም በ“ሀሳበ ለሀሳብ” የመዝናኛ ፕሮግራም የቀረቡትን ይዘታቸውንና ቅርፃቸውን መሰረት በማድረግ ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው ዋቢ መፃህፍትንና ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ሰዎች ከአባሪ ስር ጋር ተከልሰዋል::

ሌላው መነሳት ያለበት ጉዳይ ቢኖር ፕሮግራሙ ከአድማጮች የሚላኩትን የፍቅር ግጥሞች፣ ደብዳቤዎችና ሙዚቃዎችን በተቻለ መጠን ይዘታቸውንና ቅርፃቸውን ተመልክቶ

ለአድማጮች በሚስማማ መልኩ ማሻሻያ ተሰጥቶ ቢያስተላልፋቸው በይበልጥ የተሻለ እንደሚሆን ጥናቱ ያሳውቃል::

**ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው**

Recreation is any activity, either individual or collective, pursued during one's leisure times being relatively free and pleasurable, has its own appeal. It includes, play, pames, sports, athutics, amusements art forms and a vacations.

Recreation is applied in a broader can notation is the lesure activities of adults as well as children, all types of activities active as well passive. Thus the meaning of recreation… encompasses the meaning of play in general and in addition describes a community service as well as new profession.

Entertainment is something, especially a public performance that entertains. Thus an entertainment radio programme is the one that tries to keep attention of people listening. The objective of the programme to amuse or to interest.

It diverts people form their problems and anxisties, providing relaxation and entertainment. It reduces feelings of loneliness creating a sense of companionship.

Music is very important to society because it both reflects culture and creates it. Music formats change constantly because audiences are always changing… other music formats are revitalized and perpetuated to serve orginal audiences of the past or newly enthused audiences of the future.

One of the methods which enables producer of radio programmes to have variety is dialogue. Dialogue explain every situation which is even slightly confusing to compensate for he lack of visual aids.

Every since it is started listners have been writing letters to the radio programme. The records of the programme show that listeners letters were treated very seriously at the beginning. But recently letters are not given

enough attention. Only one or two listeners letters are presented in a radio program.

**አባሪ ሀ**

**ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው:- ስም ዝርዝር**

| ተ.ቁ | ስም | እድሜ | ሥራ |
|---|---|---|---|
| 1 | አቶ መልኬ ከበደ | 50 | የራዲዮ መዝናኛ ሀላፊ |
| 2 | አቶ ደረጀ ሞገስ | 55 | የራዲዮ ጣቢያው ዳሬክተር |
| 3 | አቶ ሙላት ገረመው | 35 | የራዲዮ ጣቢያው ትምህርታዊ አስተባባሪ |

**በቃለመጠይቅ የቀረቡ ጥያቄዎች**

1. ራዲዮ ጣቢያው መቼ ተጀመረ?
2. ራዲዮ ጣቢያው በማን ባለቤትነት የተመሰረተ ነው?
3. ራዲዮ ጣቢያ አጋዥ ድርጅት አለው ወይ?
4. ራዲዮ ጣቢያው እስከ የትኞቹ አጎራባች ክልሎች ይደመጣል?
5. የራዲዮ ክፍል የሰራተኞች ብዛት ምን ያህል ነው?
6. የራዲዮ ጣቢያ ዋነኛ የገቢ ምንጩ ምንድን ነው?
7. ፕሮግራሙ በስንት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ይተላለፋል?
8. የመዝናኛው ፕሮግራም የስንት ሰዓታት ጊዜን ይሸፍናል?
9. ይህ የራዲዮ ጣቢያ ከሌሎች ጣቢያዎች ልዩ የሚያደርገው ምኑ ነው?
10. የመዝናኛውን ፕሮግራም የሚያቀርቡት ጋዜጠኞች ምን ያህል ብቃት አላቸው?

# ዋቢ መፅሀፍት

በሪሁን ስመኝ:: በደሴ ራዲዮ ጣቢያ የመዝናኛ ፕሮግራም የተላለፉ የውዳሴ በአላት ግጥሞች የቅርፅ ትንተና:: ዲማጽ:: የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍል አ.አ.ዩ:: 1990 ዓ.ም

አበባው ዘውዴ:: በሬዲዮ ፋና የመዝናኛ ፕሮግራም በቀረቡ ግጥሞች የይዘት ትንተና:: ዲማጽ:: የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍል አ.አ.ዩ:: 1989 ዓ.ም

አበዛ አባተ:: በደብረማርቆስ ሬዲዮ በእሁድ የመዝናኛ ፕሮግራም የተላለፉ ግጥሞች የይዘት እና የቅርፅ ትንተና:: ዲማጽ:: የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍል አ.አ.ዩ:: 1988 ዓ.ም::

ከሳቴ ብርሃን ተሰማ:: <u>የአማርኛ መዝገበ ቃላት</u>:: አዲስ አበባ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት:: 1951 ዓ.ም ገፅ 1336::

ዓለማየሁ ሞገስ:: <u>የአማርኛ ግጥምና ቅኔ ማስተማሪያ</u>:: አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት:: 1954 ዓ.ም ገፅ 5::

ዘሪሁን አስፋው:: <u>የስነ ፅሁፍ መሰረታውያን</u>:: አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ቤት:: 1996 ዓ.ም ገፅ 73::

ይልማ ጥበቡ:: በአብዮታዊት ኢትዮጵያ ድምፅ የተላለፉ የአማርኛ ውዳሴ በዓላት መዝሙሮችና ዘፈኖች የይዘት ትንተና:: ዲማጽ:: የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍል አ.አ.ዩ:: 1976 ዓ.ም

Adams and Massay. <u>Introduction to Radio Production and Programming</u>, New York; McGraw-Hill Companies 1995.

Aylesbury, Bucks: <u>Dictionary of Literary Terms,</u> Great- Britain. Hazell Watson and Vinly Ltd. 1979.

Neumeyer, Martin Henry. <u>Leisure and Recreation.</u> New York: Brown Pub. 1892.

Robert. Maclish, <u>Radio Production.</u> 4th ed, Bath Press, Aven. 1999.

Sappora, Allenvictor. <u>The Theory of Play and Recreation.</u> New York: Ronald Press. 1961.

Solbach, Graft. <u>Radio for a Change.</u> Winfried, Koln, 1991.

Whipple, Jame: <u>How to Write for Radio:</u> McGraw Hill Book Company. Inc. London. 1938.